# የግብረገብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

### 4ኛ ክፍል

**ተርጓሚዎች**

እየሩሳለም ገርባባ

ስሪቃ ገመቹ

አበባየሁ ደምሴ

**የአርታዒዎች**

በቀለ ቀነኣ

ረታ ነገዎ

ደጀኔ ታፈሰ

**ገምጋሚ**

ደረጀ መኮንን

**ግራፍክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገላጭ ስዕል**

ብዙአየሁ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ መጽሀፍ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርና መነሻነት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስተባባሪነት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

ስለዚህ በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

**ምዕራፍ 1፡ ራስን መሆንን ማጎልበት.....1**

1.1 ራስን መሆን.....2

1.2. ራስን የመሆን ባህሪያት.....4

1.3. በራስ መኩራትን ማዳበር የሚቻልባቸው መንገዶች.....11

1.4. በራስ የመኩራት ጥቅሞች.....12

1.5. ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ.....13

1.6. ራስን ያለመሆን ውጤቶች.....15

**ምዕራፈ 2፡ ሰብአዊ መብቶች.....19**

2.1. የሰብዓዊ መብቶች ምንነት.....20

2.2. የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት.....21

2.3. ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች.....23

2.4. ሰብአዊ ክብር.....26

2.5. የሕፃናት መብቶች መከበር.....28

2.6. የሴቶች መብት መከበር.....30

2.7. የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር.....31

**ምዕራፍ 3፡ ሰላም.....36**

3.1. የሰላም ምንነት.....36

3.2 የሰላም አስፈላጊነት.....39

3.3. ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶች.....40

3.4. ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፈታት.....43

3.5. የሰላም እጦት የሚያስከትለው ጉዳት.........................................47

ምዕራፍ 4 : በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያስፈልግ መልካም ሥነ-ምግባር.................................................50

4.1. የመልካም ሥነ-ምግባር ምንነት.....................................................51

4.2. በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የመልካም ሥነ-ምግባር አስፈላጊነት......54

4.3. የዕረፍት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም...........................................56

4.4 በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት.........................................................................58

4.5. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት.......................................................64

4.6. በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚፈለጉ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች................................................................66

ምዕራፍ 5: የመቻቻል ባህል..................................................71

5. 1. የመቻቻል ባህል ምንነት.......................................................72

5.2.የመቻቻል ባህል መገለጫዎች.......................................................73

5.3. የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት.....................................................75

5.4. ለመቻቻል ባህል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች.................................76

ምዕራፍ 6፡ የባህል ብዝሃነትን ማክበር.................................80

6.1. የባህል ብዝሃነትን ማክበር.......................................................81

6.2. በባህል ልዩነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት...............................84

6.3. በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል ጥቅሞች..................................88

6.4. የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ.................................................90

# ምዕራፍ 1

## ራስን መሆንን ማጎልበት

በሦስተኛ ክፍል ሥነ-ምግባር ትምህርት ውስጥ የሥነ ምግባር እና በራስ የመተማመን ምንነት እንዲሁም ራስን እና ሌሎችን የመረዳት መሰረታዊ ነገሮችን ተምረሃል/ሻል። ይህም በራስ የመተማመን ስሜትን ለማዳበር እና ለራስህ/ሽ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖርህ/ሽ ይረዳህል/ሻል።በአራተኛ ክፍል ሥነ-ምግባር ትምህርት ደግሞ ራስን የመሆን አስፈላጊነት ለማጠናከርና ለማዳበር እንዲሁም ለራስ ከፍ ያለ ግምት ማጣት የሚያስከትለውን ውጤት ትማራለህ/ ሪያለሻ።

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-**

- ራስን የመሆን ትርጉም መግለጽ፣
- ራስን የመሆን አስፈላጊነት መግለጽ፣
- ራስን መሆንን የሚያጠናከሩ ዘዴዎችን መለየት፣
- ራስን የመሆን ባህሪያት ማሳየት፣
- ችግር ፈቺ ክህሎቶችን ማዳበር፣
- ራስን ያለመሆን የሚያስከትለውን ችግር መለየት።

# 1.1 ራስን መሆን

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ   የመማር ብቃቶች፡-

ከዚህ ትምህርት በኋላ:-

- ራስን የመሆንን   ምንነት ትገልፃለህ/ጫለሽ።
- ለራስ ከፍ ያለ ግምትን ለመጨመር  የሚረዱ ስልቶችን ትዘረዝራለህ// ሪያለሽ።



## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ራስን መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
2. ራስን የመሆን ስሜት እንዴት ማዳበር እንችላለን?

| |
|---|
| አዎ  አደርጌዋለሁ |
|  አደርገዋለሁ |
|  መስራት እችላለሁ |
|  መስራት አለብኝ |
|  እንዴት ነው የምሰራው? |
|  መስራት እፈልጋለሁ |
|  መስራት አልችልም |
| መስራት አልፈልግም |

ራስን መሆን አንድ ሰው ለራሱ የሚሰጠውን ቦታ ያሳያል። ይህም ራስን ከማክበር  ይጀምራል።ራስን መሆን አንድ ሰው የተሰጠውን ተግባር በታማኝነት እና በብቃት ማጠናቀቅን ያመለክታል።  ለምሳሌ፣  የቤት ስራ፣የክፍል ስራናፈተና  ራሱን ችሎ  በመስራት ሊገለጽ ይችላል። ይህም  አንድ ሰው

አዎንታዊ አመለካከትን ፣ በራስ መተማመንን ለማዳበርና በችሎታው እንዲኮራ ይረዳዋል።

## የጉዳይ ጥናት

ቤካ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነው። አብዛኛ ጊዜውን መጽሐፍ በማንበብ ያሳልፋል፡ ፡ በትርፍ ሰዓቱ እግር ኳስ ይጫወታል። ጠንካራ ተማሪ ስለሆነ ሲያጠናም ሆነ ሲጫወት በመርሃ ግብሩ ወይም በፕሮግራሙ መሠረት ነው። እንዲሁም ትምህርቱን በትኩረት ይከታተላል፡፡ የቤት ስራውንም በሰዓቱ ያጠናቅቃል። የተሰጠውን ማንኛውንም ተግባር ማከናወን እንዳለበት ያምናል። ጓደኞቹ የቤት ሥራ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ይመክራቸዋል። ፈተና ማጭበርበርንም ሆነ መስረቅ አጥብቆ ያወግዛል። የፈተና ጊዜ ሲቃረብ እራሱን ማዘጋጀት ይጀምራል። በፈተና ቀን በተረጋጋ ሁኔታ ስለሚሰራ ጥሩ ውጤት ያስመዘግባል። ቤካ ጠንክሮ በመስራቱና ጥሩ ውጤት በማስመዝገቡ በጣም ደስተኛ እና በራሱ የሚኮራ ነው።



ምስል 1.1. በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች ጠንክረው ይማራሉ

## ተግባር 1.1

**ከላይ ባነበብከው የጉዳይ ጥናት ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ**

1. ከዚህ አጭር የጉዳይ ጥናት ምን ተማርክ/ሽ ?
2. ጠንካራ ተማሪ እንደሆንክ/ሽ ታስባለህ/ብያለሽ?
3. በምን ዓይነትሥራዎች ቤተሰብህን/ሽን ታግዛለህ/ዢያለሽ?

# 1.2. ራስን የመሆን ባህሪያት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ :-

- ራስን የመሆን ባህሪያትን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ
- በራስ የመተማመን ባህሪያትን ታሳያለህ/ይለሽ

## የግንዛቤ ጥያቄ

- ራስን የመሆን ባህሪያት ምንድን ናቸው?

### ቢፍቱ እና ጫላ

ቢፍቱ እና ጫላ የትምህርት ቤት ጓደኛሞች ሲሆኑ የተለያየ ችሎታ እና ልምድ አላቸው። ቢፍቱ በማህበራዊ ስራ ጥሩ ልምድ አላት። እንዲሁም ከቤተሰቦቿ፣ ከጓደኞቿና ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር በንቃት ትሳተፋለች። ስለዚህ ቢፍቱ ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት በመመሰረት ትታወቃለች። በሌላ በኩል ደግሞ ጫላ የተለያዩ ልምዶችና ክህሎቶች አሉት። ከስኬቶቹና ውድቀቶቹ የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን ይማራል። ጫላ ጠንካራና ውጤታማ ተማሪ ሲሆን ችግሮችን ተቋቁሞ አላማውን ማሳካት የሚችል ነው። ሁሉንም የትምህርት ሥራውን በራስ በመተማመን ስሜትና ራሱን በመቻል የሚሰራ ነው። ይህም

ስኬት አስገኝቶለታል።

## ተግባር 1.2.

ባነበብከው/ሽው የቢፍቱና ጫላ ታሪክ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. የቢፍቱና የጫላ ችሎታና ልምድ ምን ምንድናቸው?
2. የጫላ በራስ የመተማመን ባህሪያት ምንድናቸው?

ራስን መሆን የተለያዩ ባህሪያት ቢኖረውም ዋና ዋናዎቹ ራስን መቻል፣ በራስ መተማመን እና ራስን መግዛት ናቸው።

### ሀ. ራስን መቻል

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ራስን መቻል ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጥገኝነት ወይም ራስን አለመቻል ምንድን ነው?

እራስን መቻል አንድ ሰው በሌሎች ላይ ጥገኛ ሳይሆን አንድን ስራ ለመስራት እና የራሱን ችግሮች በራሱ መፍታት መቻል ነው።

### የጉዳይ ጥናት 1. 1

ጫልቱ የ4ኛ ክፍል ጎበዝ ተማሪ ነች። የቤት ስራዋን በሰዓቱ ትሰራለች።ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በትኩረት ታጠናለች። ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት የተለያዩ መጽሐፍት ታነባለች። ጫልቱ ያልገባትን አስተማሪዎቿንና ጓደኞቿን ትጠይቃለች። በተጨማሪም ፈተና ሳይደርስ ቀድማ ትዘጋጃለች ። ይህም በፈተና ጊዜ መረጋጋትን እና በራስ መተማመንን ሰጥቷታል። ስለዚህ ጫልቱ ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ በመስራት ጥሩ ውጤት ታስመዘግባለች።



ምስል 1.2. በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች ጠንክረው ይሳተፋሉ

## ተግባር 1.3

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ

1. ተማሪ ጫልቱ በችሎታዋ ታምናለች? እንዴት?
2. በራስ የሚተማመን ሰው በራሱ ብቃት ያምናል ብለህ/ ሽ ታምናለህ/ ኛለሽ?
3. ጫልቱ ያልተረዳችውን ነገር ጓደኞቿን መጠየቋ ጥገኝንት ነው ብለህ ታስባለህ/ሽ? ለምን?
4. ራስን የመቻል ሁለት ጥቅሞች ግለጽ/ጪ።

## ለ. በራስ መተማመን

### የግንዛቤ ጥያቄ

- በራስ መተማመን ማለት ምን ማለት ነው?

በራስ መተማመን ማለት አንድ ሰው አንድን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል ብቃት እንዳለው በራሱ ማመን ነው። ይህም አንድ ሰው የራሱን ብቃት በማወቅና ጠንክሮ ለመስራት ያለው ተነሳሽነት ነው። በራሱ የሚተማመን ተማሪ በክፍል ውስጥ በትኩረት ይሳተፋል፣ የቤት ስራና የቡድን ስራ ጠንክሮ ይሰራል። የራሱ የጥናት ዕቅድ በማውጣት ያጠናል። በራሱ የሚተማመን ሰው ችግሮችን ለመፍታት አስቀድሞ የሚዘጋጅ፣ ዕድሎችን የሚጠቀም፣ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ሀላፊነቱን የሚወስድና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መሥራት የሚችል ሰው ነው። ይህም በራሱ የሚተማመን ሰው ባህሪ ነው። “ከደፋር ሰው ዘፈን ያምራል” እንደሚባለው በራስ የመተማመን ስሜት ካለን ያለ ምንም ፍርሃት ነገሮችን ማሳካት እንችላለን።

### አበበች እና ወንድሟ

አበበች የ4ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ዝቅተኛ ነጥብ ታስመዝግባለች። በክፍል ውስጥ የፍርሀት ስሜትና የመጨነቅ ባህሪይ ታሳያለች። ወንድሟ ሌንጮ በዚህ ውጤቷ በጣም ይናደዳል። ስለዚህ ሁልጊዜ ጠንክራ እንድታጠና ይመክራታል።ቤተሰቦቿም ከተጨማሪ የቤት ውስጥ ሥራዎች ነፃ በማድርግና አስፈላጊውን የትምህርት ቁሳቁስ በማቅረብ ጠንክራ እንዲትማር ማበረታታት ጀመሩ። እሷም የቤተሰቦቿን ምክር በመስማት በርትታ ማጥናትና የቤት ስራዋን መስራት ቀጠለች። በተጨማሪም የተለያዩ የማጣቀሻ መጽሐፍትን ማጥናት ጀመረች። እንዲሁም ወንድሟን፣ አስተማሪዎቿን እና የክፍል ጓደኞቿን በመጠየቅ የከበዷትን ትምህርቶች ቀስ በቀስ በማሻሻል ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ቻለች። ወንድሟ ለንጮ የእኔ እርዳታ ሁል ጊዜ ያስፈልጊሻል ሰላት እሷ ግን “አይ! ስትመክረኝ አዳምጫሀለሁ፣ አሁን ግን ያንተ እርዳታ አያስፈልገኝም፣ራሴ መሥራት ችያለሁ” አለች። ወንድሟም

በእህቱ በራስ የመተማመን ቸሎታ በማዳበሯ በጣም ተደሰተ።



ምስል1.3. በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች ታማኝ ናቸው

## ተግባር 1.4.

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ

1. ከአበበች እና ሌንጮ ታሪክ ምን ተገናዘባችሁ? ተማራችሁ?
2. በሚከተሉት ባህሪያት ላይ ተወያዩና ለክፍል ተማሪዎች አስረዱቸው!

   ሀ) ዓይንአፋርነት ለ) ፍርሃት ሐ) ጭንቀት
3. አበበች በራስ የመተማመን ባህሪን ያዳበረችው እንዴት ነው?
4. በራስ መተማመን ለመማር ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
5. በራስ መተማመንን ለማሻሻል ምን ምን ማድረግ አለብኝ ትላለህ/ሽ?

## ሐ. ራስን መግዛት



### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ራስን መግዛት ምንድነው?
2. ራስን መግዛት በሚለዉ ሀሳብ ትስማማለህ/ሽ?

### ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ምን ትማራችሁ?

1. "ራሱን የማይገዛ ሰው ልጓም እንደሌለው ፈረስ ነው"
2. " ረሃብን ብቻ ሳይሆን ጥጋብንም እችላለሁ" አሉ አባ ጅፋር
3. "ራሱን የማይገዛ ሰው ሰውን አያከብርም"

ራስን መግዛት ማለት ሌሎችን ከሚጎዱ ነገሮች መራቅና አለማድረግ ነው። ለምሳሌ ከጓደኞቻችን ጋር ስንጫወት በቃላችን እንዳንጎዳቸው እራሳችንን መቆጣጠር አለብን። ስለዚህ ራስን የመግዛት ችሎታ ማዳበር አስፈላጊ ነዉ ።

### የሚከተለዉን አጭር ትረካ አንብባችሁ አስተውሉ

አንድ ቀን ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲወጡ እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ሳለ አንድ እንግዳ ሰው ተቀላቀላቸው። ይህ ሰው ያለ ተማሪዎቹ ፍቃድ ወደ እግር ኳስ ጨዋታ ከእነሱ ጋር እንዲሄዱ ተማሪዎቹን ጠየቀ። ተማሪዎቹ አብረው ለመሄድ ፍቃደኛ ሳይሆኑ ወደ ቤታቸው ሄዱ። ነገር ግን ፖሊስ ግለሰቡ የሕፃናት አዘዋዋሪ ፣ ወንጀለኛ በመሆኑ ለአመታት ሲፈልግ እንደነበረ ገልጾ በቁጥጥር ሥር አውሎታል።



ምስል 1.4 በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች የተረጋጉ ናቸው

## ተግባር 1.5

1. እላይ ከተገለጸው ትረካ ምን ተማራችሁ?
2. የእኩዮቻችሁን ተጽዕኖ ለመቋቋምና ራስን ለመግዛት ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?
3. ራስህን /ሽን የመቆጣጠር ችሎታ አለህ/ሽ?

# 1.3. በራስ መኩራትን ማዳበር የሚቻልባቸው መንገዶች

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-

ከዚህ ትምህርት በኋላ :-

- በራስ የመተማመን ባህሪያትን እንዴት ማዳበር እንደሚቻል ትገልጻለህ/ሽ
- በራስ የመተማመን ባህሪያትን ታሳያለህ/ሽ፡፡

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

ለራስህ ያለህን ግምት ለማጠናከር የሚትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር?

የአንድን ሰው በራስ መኩራትን ለማጠናከር የሚረዱት የሚከተሉት ናቸው። እነሱም

- የራስን ችሎታ መረዳት እና ማድነቅ
- በፈገግታ እና ዓይን ለዓይን በመተያየት በራስ መተማመን መነጋገር
- በእችላሁ ስሜት መሥራት
- መልካም ስነ ምግባር ካላቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር
- ማንነትህን የሚያከብሩ ጓደኞችን ማፍራት ናቸዉ።

## የቡድን ውይይት

ከላይ ካነበባችሁት የአንድን ሰው በራስ መተማመን የሚያጎለብቱትን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

## 1.4. በራስ የመኩራት ጥቅሞች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡**

ከዚህ ትምህርት በኋላ :-

- በራስ የመኩራት አስፈላጊነት ታደንቃለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ለራስ ከፍ ያለ ግምት መስጠት ህይወታችንን ሊያሻሽለው የሚችለው እንዴት ነዉ?
2. ራስን መሆን በትምህርት ስኬት ውስጥ ያለውን ሚና ዘርዝር ።

ራስን መሆን የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት.

- ለራስ ማስብ እና በአዎንታዊ ስሜቶች መኖር
- በራስ የመተማመንና ራስን የማክበርን ስሜት ያዳብራሉ
- የራስ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን ለይቶ ማወቅ
- በአዎንታዊ መልኩ እንዲናስብ ያስችለናል።

# 1.5. ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-

- ተግዳሮቶችን መቋቋም የሚያስችሉ ችሎታዎችን ያዳብራሉ
- ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ ታሳያለህ/ሽ

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ለአንተ/ለአንቺ ችግር ምንድነው?
2. በህይወታችሁ ውስጥ የሚያጋጥሟችሁን ችግሮች እንዴት ትቋቋሟላችሁ?

በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ብዙ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች የህይወት ፈተናዎችን በልቤ ሙሉነት ሲያሸንፉ ሌሎች ደግሞ በችግርና በህይወት ፈተና ይሸነፋሉ። አንዳንዴ ችግር ወይም ፈተና የዕድገት ዕድል ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ችግሮች ወይም ፈተናዎች እውነትን የመረዳት ችሎታችንን እንዲናዳብር ይረዱናል። በአግባቡ ከተጠቀምንበት የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለማሸነፍ የሚያስችል አቅም ይፈጥሩልናል።

የራሳችንን የግል ችግሮች ለመፍታት የሚረዱን መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

እነሱም፡

- በአከባቢያችን ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች መፈተሽ
- ያሉንን ሀብቶች ጠንቅቆ ማወቅ
- የራስን ችሎታ ማወቅ እና እርምጃ መውሰድ ናቸው።

# የኤሊዎች ውድድር

አንድ ቀን ብዙ ኤሊዎች ለመወዳደር ወጡ ይባላል። ውድድራቸውም ትልቅ ተራራ ላይ ቀድሞ ለመውጣት ነበር። ውድድሩም ይህን ትልቅ ተራራ መውጣትና በተራራው ጫፍ ላይ ያለውን አረንጓዴ እና ለምለም ሣር መብላት ነበር። ኤሊዎቹ ሩጫቸውን ጀምረው ወደ ተራራው መሃል ሲደርሱ ሰዎች ጮኹባቸው።"ተመለሱ ወደዚህ ተራራ መዉጣት አትችሉም፣ ታልቃላቹ ፣ ወደ ተራራው ጫፍ ቢትደርሱም እንኳን አዲስ ነገር የለም›› እያሉ ጮሁባቸዉ።

ወዲያውም ብዙዎቹ ኤሊዎች ወደ ተራራው መሃል ደርሰው በሰዎች አስተያየትና ጩሄት ተስፋ በመቁረጥ ወደ ኋላቸው ተመለሱ። ነገር ግን አንድ ኤሊ በዝግታ እየሄደች ከብዙ ጥረት በኋላ ወደ ተራራው ጫፍ ደረሰች። በተራራው ጫፍ ላይ ያለዉን ለምለም ሣር አገኘችና ሳሩን ብቻዋን መብላቷን ቀጠለች።

ከዚያም አንድ አሞራ መጥቶ ኤሊውን፣ "ጓደኞችህ ሁሉ ወደ ኋላ ሲመለሱ አንቺ እንዴት ወደዚህ ትልቅ ተራራ ወጣሽ?" አላት። ደጋግሞ ቢጠይቃትም ኤሊው መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ አልሆነችም።

በመጨረሻም, ኤሊው የመስማት ችግር እንዳለባት እና አሞራው የሚናገረውን መስማት እንደማትችል ነገረችው። ስለዚህ ስላሰማች የሰዎች ተስፋ አስቆራጭ ንግግር አላስቀራትም። የኤሊዋ የመስማት ችግር ለስኬታማነቷ ዕድል ነበር። ይህ ማለት አንዳንድ ጊዜ ችግሮች ለስኬት ዕድሎች ይሆናሉ ማለት ነው። ስለዚህ ከተነሳችሁበት ዓላማ ወደ ኋላ መመለስ ተገቢ አይደለም።



## ተግባር 1.6

1. ዉድድሩን ያቋረጡት ኤሊዎች ራስ የመሆን ባህሪይ የላቸውም?
2. የውድድሩ አሸናፊ ኤሊ መስማት አለመቻሏ ለስኬት ዕድል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. ከዚህ ምን ተማራችሁ?

# 1.6. ራስን ያለመሆን ውጤቶች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

- ራስን ያለመሆን የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ትገልጻለህ/ሽ።
- በራስ መተማመን የሌላቸውን ሰዎች ባህሪያትን ትለያለህ/ሽ

## የግንዛበ ጥያቄ

- ራስን ያለመሆን ባህሪያት ምንድን ናቸው?

በራስ መተማመን የሌላቸው ሰዎች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው።

እነሱም፤-

- በራስ የመተማመን ባህሪይ ማጣት፤
- ራስን እንደ ተሸናፊ ማየት፤
- የራሰን ስህተት አለመቀበል፤
- ላለመሳሳት በመፍርሃት ከተሳትፎ መቆጠብ፤
- የትምህርት ፍላጎት ማጣት፤
- ማድረግ አልችልም የሚል አመለካከት መኖር ናቸው።

## ተግባር 1.7

ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት በአንድ ሰው ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

# ማጠቃለያ

ራስን መሆን ራስን ከማክበር ይጀምራል።ራስ መሆን አንድ ሰው የተሰጠውን ተግባር በታማኝነትና በብቃት ማጠናቀቅ ነዉ። ለምሳሌ የቤት ስራን፣ ፈተናን ፣ በተሙከራዎችን በአግባቡ በመስራት ይገለጻል። ይህ አዎንታዊ አመለካከትንና በራስ የመተማመንን ለማዳበር እና ስዎች በችሎታቸው እንዲኮሩ ይረዳቸዋል። ራስን መሆን አንድ ሰው ስለራሱ ችሎታ እንዲያሰብ እና ስለራሱ ጥሩ ስሜት እንዲሰማው ያግዛል። ምንም እንኳን ራስን መሆን የተለያዩ ባህሪያት ቢኖረውም፣ በጣም አስፈላጊዎቹ ራስን መግዛት፣ በራስ መተማመንና ራስን መቻል ናቸው።

## የቃላት ፍቺ

**ራስን መሆን** - ለራስ ጥሩ ስሜት ማዳበርና በራስ ችሎታ መተማመን

**እራስን መቻል** - ስራን ራስን ችሎ በተናጥል መስራት እና ችግሮችን መፍታት

**በራስ መተማመን** - አንድን ተግባር ለማከናወን ችሎታ እና ቁርጠኝነት መኖር.

**እንቅፋት** - አንድ ሰው ግቦቹ ላይ እንዳይደርስ የሚከለክሉ መሰናክሎችና ሁኔታዎች ናቸው፡፡

**ራስን መግዛት** - ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን ከመፈጸም መቆጠብ.

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡** ትክክለኛውን ዓረፍተ ነገር እውነት ትክክል ያልሆነውን ዓረፍተ ነገር ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ።

1. ራስን መሆን ለራስ ጥሩ ስሜት ማዳበርና በራስ ችሎታ ማመን ነዉ
2. በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ከሌሎች ጋር በመደጋገፍ ይኖራሉ።
3. ራሱን እንዳይችል ስለሚያደርገዉ ሰውን መርዳት ጥሩ አይደለም ።

**ክፍል ሁለት፡** በአምድ "ለ" ስር ያለውን ቃላቶች ወይም ሐረጎች ከአምድ "ሀ" ስር ጋር አዛምዱ።

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| 1. | የማያስደስቱንን ነገሮችን ከመሥራት መቆጠብ | ሀ. በራስ ማመን |
| 2. | በራስ ችሎታ በመተማመን ማከናወን | ለ. ጥገኝነት |
| 3. | በሌሎች ተጽዕኖ ውሳኔዎችን መወሰን | ሐ. እራስን መቻል |
| 4. | በራስ ችሎታ መመራት | መ. እራስን መግዛት |

**ክፍል ሦስት፡** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ

1. ከሚከተሉት ውስጥ ራስ መግዛትን ለማዳበር የሚረዳህ/ሽ የትኛው ነው?

   ሀ. የራስን የበላይነት ማረጋገጥ

   ለ. በራስ የመተማመን ባህሪይ

   ሐ. ከሌሎች እርዳታ መፈለግ

   መ. ብቃት እንደለሌ አምኖ መቀበል

2. ከሚከተሉት ውስጥ ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ምልክት የትኛው ነው?

ሀ/ በስራው የሚረካ

ለ. አብዛኛ ጊዜውን ብቻውን የሚያሳልፍ

ሐ/ ችሎታ እንዳለው የሚያምን

መ/ የራሱን ውድቀቶች ሁል ጊዜ የሚያውቅ

3. በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የሌሎችን አስተያየት እና ትችት መቀበል

ለ. በአዳዲስ ሀሳቦች መኖር

ሐ. የሌሎችን አስተያየት በቅንነት ማዳመጥ

መ. ማታለል

4. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ጥገኝነት ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የጥገኝነት ህይወት ክብር ይሰጣል።

ለ.ጥገኝነት የበታችነት ስሜት ይፈጥራል።

ሐ. ጥገኝነት ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሳሪያ ነው.

መ. ጥገኝነት የትብብር አካል ነው።

5. ከሚከተሉት ውስጥ የራስ መተማመን ገላጭ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በራስ የመተማመን

ለ. ራስን መግዛት

ሐ. ራስን መቻል

መ. ራስን መናቅ

# ምዕራፍ 2

# ሰብአዊ መብቶች

በባለፈው ምዕራፍ በራስ መተማመንን ተምረሃል/ሻል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለሰብዓዊ መብቶች ምንነት፤ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት፤ ሰብአዊ መብቶችና ግዴታዎችን ፤ሰብአዊ ክብር፤ የህጻናት፤ የሰቶችና የአካል ጉዳተኞች መብቶችን ትማራለህ/ሽ፡፡

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:-

- የሰብአዊ መብቶችን ጽንሰ-ሀሳብ ማብራራት፣
- የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነትን መግለፅ፣
- በመብቶች እና ግዴታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት መለየት፣
- ሰብዓዊነትን ማክበር፣
- የህጻናት፤ የሴቶችና እና አካል ጉዳተኞችን፣ መብቶች መግለጽ፣
- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ባህሪን ማሳየት።

## 2.1. የሰብዓዊ መብቶች ምንነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡**

- ሰብአዊ መብቶችን ትገልጻለህ/ሽ።
- የሰብአዊ መብቶች ምሳሌዎችን ትናገራለህ/ሽ።

### ተግባር 2.1

1. ሰብአዊ መብቶች ምንድናቸው?

2. ቢያንስ ሶስት የሰብአዊ መብቶች ምሳሌዎችን ዘርዝር/ሪ።




ስዕል 2.1. ሰብአዊ መብቶች

ሰብአዊ መብቶች ሁሉም ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ የሚጎናጸፋቸዉ መሰረታዊ መብቶች ናቸው። ለሰብአዊ መብቶች ብቸኛው መለኪያውና መስፈርቱ ሰው መሆን ብቻ ነው። ማንም ሰው በዘር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔርና በፖለቲካ አመለካከቱ፣ ወዘተ ሳይለይ ይህን መብት አለው። ሰብአዊ መብቶች በህይወት

የመኖር መብት ፣ የእኩልነት መብት፣ የደህንነት መብት፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣ የመማር መብት እና የመሳሰሉትን መብቶች የሚያጠቃልል ነዉ ፡፡ ሰብአዊ መብቶችን መጣስ ከሞራልም ሆነ ከህግ አንፃር ተቀባይነት የለውም

### ተግባር 2.2.

ባዶ ቦታውን በትክክለኛ ቃል ሙላ/ይ.

- ሰብአዊ መብት መስፈርቱ ________ መሆን ብቻ ነው።

## 2.2. የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት ትዘረዝራለህ/ሽ
- ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ዋጋ ትሰጣለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. የሰብአዊ መብቶች መከበር ለህብረተሰቡ ምን አስተዋጽኦ አለው?
2. የሌሎችን ሰዎች መብት ማክበርና ሌሎች ሰዎች የአንተን (ቺ) መብት እንዲያከብሩ በመጠበቅ መካከል ግንኙነት አለ?
3. በትምህርት ቤትህ/ሽ ግቢ እና በክፍል ውስጥ ሰብአዊ መብቶችን የማክበርን አስፈላጊነት አብራራ/ሪ።

ሁሉም ሰው በነጻነት እና በሙሉ ሰብአዊ ክብር ይወለዳል፡፡ ይህ ተፈጥሯዊ መብት ደግሞ ሊከበርና በሕግ ጥበቃ ልያገኝ ይገባል።

እነዚህን ሰብአዊ መብቶች የማክበር አስፈላጊነት፡

- ተቻችሎ አብሮ ለመኖር፣
- ስራን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን፣

- ከጭቆና የጸዳ ማህበረሰብ ለማፍራት፣
- ሃሳብን በነጻነት ለመግለጽ ፣
- የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ፣
- የመንቀሳቀስ ነፃነትን ለማረጋገጥ፣
- ከተጽዕኖ ነጻ ለመሆንና የመሳሰሉት ናቸው።

## ተግባር 2.3

**ትክክል የሆነውን ዓረፍተ ነገር እውነት ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ።**

1. ሰብአዊ መብት ሃሳብን በነፃነት በመግለጽ በሰላም መኖርን ያጎናፅፈናል::
2. ሁሉም የሰው ልጆች በሙሉ ነፃነት፣ በክብር እና በእኩልነት ይወለዳሉ።
3. የሰብአዊ መብት መከበር ለሰላም አስፈላጊ ነው።
4. የሰብአዊ መብት መከበር ከተጽዕኖ የፀዳ ማህበረሰብን ለመገንባት ይረዳል።

# 2.3. ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

- ሰብአዊ መብቶችና ግዴታዎችን ታነጻጽራለህ/ሽ።
- ሰብአዊ መብቶችና ግዴታዎችን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡.
- በመብቶችና እና ግዴታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ትገልጻለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. በመብትና ግዴታ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
2. ሰዎች ግዴታቸውን ሳይወጡ መብታቸውን ብቻ ቢጠይቁ ምን ሊፈጠር ይችላል?

መብትና ግዴታ የማይነጣጠሉና ሁለቱም ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ . ማንኛውም ሰው መብቱን ሲጠይቅ ግዴታም ጭምር እንዳለው መገንዘብ አለበት፡፡ መብቱን ሲጠቀምም የሌሎችን ሰዎች መብት የማክበር ግዴታ አለበት። ለምሳሌ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብቱን ሲጠቀም የሌሎችን መብቶች የማክበር ግዴታ አለበት። ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን በመጠቀም ሌላውን ሰው መሳደብ አይችልም። ሰውን መሳደብ የሞራል እና የህግ ጥሰት ነው። መንግሥት እነዚህን መብቶች የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታ አለበት። ከዚህ በታች ሊኖረህ/ሽ የሚችሉ መብቶች እና ግዴታዎች ተዘርዝረዋል።

### መብቶች

- በሰላም የመኖር መብት
- ጥያቄ የመጠየቅ መብት
- በቂ ምግብ የማግኘት መብት
- የመማር መብት

## ግዴታዎች

- እናትና አባትን ማክበር
- አረጋዊያንን ማክበር
- መምህራንን ማክበር
- የትምህርት ቤት ህጎችንና ደንቦችን ማክበር
- አላስፈላግ ቃላትን ከመናገር መቆጠብ
- ጎረቤትን ማክበር
- ቤተሰብን ማገዝ
- ከጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች መቆጠብ
- አካባቢን ማጽዳት
- የቤት ስራ እና የክፍል ሥራ ፈተናን ራስን ችሎ መስራት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

መብት እና ግዴታ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡. ግዴታውን የሚወጣ መብቱን ይጠቀማል

ግዴታውን የማይወጣ መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ቤተሰብህ/ሽ እንድ‌ታደርግ/ጊ

ያዘዙህን/ሽን ከፈፀምክ/ሽ ከጓደኞችህ/ሽ ጋር እንድትጫወት/ቺ፣ ይፈቅዱልሃል/ሻል፡፡

ቆሻሻን ከአካባቢ ማጽዳት ጽዱ አካባቢ ውስጥ እንዲትኖር/ሪ ያስችልሃል/ሻል።

## ተግባር 2.4

- “መብት እና ግዴታ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው” የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል?



ምስል 2.2፡ ተማሪዎች ክፍላቸውን ሲያጸዱ።

## ተግባር 2.5

በሚቀጥለው ሰንጠረዥ መብቶችና ግዴታዎችን በመለየት ሙላ/ይ.

| ተ/ቁ | መብት | ግዴታ |
|---|---|---|
| 1 | መጫወት | የትምህርት ቤት ህጎችን እና መመሪያዎችን መከተል |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

## 2.4. ሰብአዊ ክብር

**ቢያንስ ልትገነዘቧቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች:**

- ሰብአዊ ክብርን ትገልጻለህ/ሽ።
- ሰብአዊነትን ታከብራለህ/ሽ።
- ሰብአዊ መብት ጥሰትን ታወግዛለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ሰብአዊ ክብር ምንድን ነው?
2. የክፍል ጓደኞችህን/ሽን ታከብራለህ/ሽ?



ምስል 2.3: ሰብአዊነትን ማክበር(አረጋዊያን መንከባከብ)

ሰብአዊንትን ማክበር ማለት ለራስና ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠት ማለት ነው። ለራሳችን ክብር እንደሚንፈልግ ሁሉ ሌሎችንም ማክበር አለብን። “ስታከብር ትከበራለህ” የሚል አባባል አለ። ይህ ማለት ለሌሎች አክብሮት ካለን ሌሎች ያከብሩናል ማለት ነው። ስለዚህ ቤተሰብህን፣ ጓደኞችህንና ጎረቤቶችህን የሚታከብር ከሆነ በእነርሱ ዘንድ ትከብራለህ ማለት ነው። ሰብአዊነትን የሚጋፉ ድርጊቶች ስድብ፣ አድልዎ፣ ንቀት፣ የወንጀል ድርግቶች፣ ጦርነት እና የጉልበት ብዝበዛ ናቸው፡፡

ለሌሎች አክብሮት የሚናሳይባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

- ለሰብአዊነት እውቅና በመስጠት;
- ለሰብአዊነት ርህራሄ በማሳየት;
- የሰዎችን ሃሳብ በማድመጥና በማበረታታት;
- ለሰዎች በጎ አስተዋጽዖ እውቅና መስጠትና የመሳሰሉት ናቸው።

## ተግባር 2.6

ባዶ ቦታውን በትክክለኛ ሐረግ ሙላ/ይ

1. ____________ ለሰው ልጅ ሁሉ ሊሰጠውና ሊታወቅለት የሚገባው ነው።
2. ሰብአዊነትን የሚጋፉ ድርጊቶች፡- ____________፣ ____________፣ ____________፣ ____________።

# 2.5. የሕፃናት መብቶች መከበር

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡

- የሕፃናት መብቶችን ትዘረዝራለህ/ሽ
- መብቶችህን ትተገብራለህ/ሽ?

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. የህጻናት መብቶችን ዘርዝር/ሪ
2. እንደልጅነትህ/ሽ ምን አይነት መብቶች አለህ/ሽ?

በኢትዮጵያ ህግ መሰረት እድሜው ከ18 አመት በታች የሆነ ሰው ህጻን ይባላል። ህጻናት የራሳቸው የሆኑ መብቶች አሏቸው፡፡. የህጻናት መብቶች በጾታ፣በዘር፣ በቋንቋ፣ በእድሜና ሀይማኖት ሳይለዩ የሁሉም ህጻናት መብቶች ናቸው።

ማንኛውም ህጻን የሚከተሉትን መብቶች አሉት።

- የጤና አገልግሎት እና እንክብካቤ የማግኘት፣
- ነፃ የመሠረታዊ ትምህርት ዕድል የማግኘት
- በእንክብካቤ የማደግ፣
- በጦርነት ጊዜ ልዩ ጥበቃ የማግኘት;
- ከአቅም በላይ ከሆኑ ስራዎች ነጻ የመሆን፣
- የመጫወት ነጻነት፣
- ከወላጆቻቸውና ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር የመኖርና የማደግ መብት አሏቸው።



ምስል 2.4: ህጻናት የመጫወት መብት አላቸው

## ተግባር 2.7

1. የህጻናትን መብቶችየማክበር ጥቅሞች ዘርዝር/ሪ?
2. በሚትኖርበት/ሪበት አካባቢ የህጻናትን መብቶች የማክበር ግዴታ እንዴት ይተገበራል?

## 2.6. የሴቶች መብት መከበር

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡**

- የሴቶችን መብት ትዘረዝራለህ/ሽ።
- የሴቶችን መብት ታከብራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ሴቶች ከወንዶች እኩል ማንኛውንም ሥራ በየትኛውም ቦታ መሥራት ይችላሉ በሚለው ሀሳብ ትስማማለህ/ሽ?
2. የሴቶችን መብቶች ዘርዝር/ሪ?

በኦሮሞ ባህል ሴቶች ይከበራሉ፡፡የሴቶችን መብት ማክበር ከማህበረሰባችን መልካም እሴቶች ውስጥ አንዱ ነው። ስለዚህ የሴቶችን መብት መጣስ ጎጂ ባህል ነው። በጾታ እኩልነት ማመንና ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡. ሁሉም ዜጋ የሴቶችንና የወንዶችን እኩልነት በመቀበልና በመደገፍ የፆታ መድልዎን መታገል አለበት ።የሴቶች መብቶች መከበር ለቤተሰብ ህይወት መሻሻል፣ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ደህንነት አስፈላጊ ነው። የሴቶችን መብቶች ማወቅና ማክበር ማለት የእህቶችንና የእናቶችን መብት ማወቅ ማክበር ማለት ነው።



ምስል 2.5፡ ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት አላቸው

## ተግባር 2.8

1. የሴቶችን መሰረታዊ መብቶች ዘርዝር/ሪ።
2. ያታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ማን መታገል አለበት?

# 2.7. የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡**

- የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ትዘረዝራለህ/ሽ።
- የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ታከብራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄዎች፡-

1. አካል ጉዳተኝነት ምንድን ነው?
2. ለአካል ጉዳተኝነት የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ግለጽ/ጭ.



ምስል 2.6፡ አካል ጉዳተኞች የመማር መብት አላቸው

አካላዊ ጉዳት የአንድን ሰው እንቅስቃሴ አካላዊ ችሎታ ጥንካሬንና ጤንነትን የሚጎዳ ነው.፡፡ አካል ጉዳተኞች ሌሎች ሰዎች ያሏቸውን መብቶች አሏቸው። አካል ጉዳተኞች ሙሉ ክብርና እና የመማር መብት አላቸው።

ስለዚህ አካል ጉዳተኞች ከቤተሰቦቻቸው፣ከአሳዳጊዎቻቸው ፣ከመንግስት፣ ከማህበረሰቡ እና ከሰብአዊ የእርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ ማግኘት አለባቸው። የተለያዩ የትምህርት ቁሳቁሶች እንደ ብሬል፣ ተሽከርካሪ ወንበሮች (ዊልቸር) እና ሌሎች የተለያዩ መሳሪያዎችን ማግኘት አለባቸው። ሁሉም ህንጻዎች፣ መሳሪያዎች፣ ምርቶች፣ መገልገያዎች፣ መሠረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂዎች እና አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ በሆነ መንገድ መዘርጋት አለባቸው።

የገበያ አገልግሎቶች እና የተለያዩ የስራ አካባቢዎች ክፍት፣ አካታች እና ምቹ ለአካል ጉዳተኞች ዕድል የሚሰጡ መሆን አለባቸው። አንድ ሰው ሲወለድ ወይም ከተወለደ በኋላ በተለያዩ ሁኔታዎች አካል ጉዳተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአደጋ፣ በበሽታ፣ በህክምና ጊዜ በሚፈጠሩ ስህተቶች ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

## ተግባር 2.9

- የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ዘርዝር/ሪ

### የጉዳይ ጥናት

ሎከ መስማት የተሳናት ተማሪ ነች፡፡ በክፍል ውስጥ ለመሳተፍ ትቸገራለች፡፡ መምህራኖቿም ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት የአስተማሪዎቿን መመሪያና መልእክት መስማት እንዲትችል በክፍል ውስጥ ፊት ለፊት ያስቀምጧታል። በተጨማሪም፣ ትምህርት ቤቱ የማዳመጫ መሳሪያዎችን እንድትጠቀም ያግዛታል። የክፍል ጓደኞቿም ይወዷታል ደግሞም ያከብሯታል፡፡ በትምህርቷም ተሳክቶላት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች።

## ተግባር 2.10

1. ከሎኮ ስኬት ምን ተማርክ/ሽ?
2. ለሎኮ ይሰጥ የነበረው ድጋፍ ምን አይነት ድጋፍ ነው?
3. ሰዎች ሎኮን የበለጠ እንዴት መርዳት ይችላሉ?

## ማጠቃለያ

ሰብአዊነት ተፈጥሮአዊ ነው።ሁሉንም ሰው ይመለከታል፡፡ መብቶች እና ግዴታዎች የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ስለ መብት ሲናነሳ ግዴታችንንም መዘንጋት የለብንም። ስለዚህ ማንኛውም ሰው መብቱን ሲጠቀም የሌሎች ሰዎችን መብት መጣስ የለበትም። የሰብአዊ መብቶች መከበር ሰዎች በሰላም አብሮ እንዲኖሩ ያደርጋል። መብትን ማክበር ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶችንና ጭቆናን መታገል ማለት ነው። ማህበረሰቡ የአካል ጉዳተኞች ፣የህፃናት እና የሴቶች መብቶችን ማክበር አለበት፡፡

አካል ጉዳተኝነት በማንኛውም ሰው ላይ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችል ክስተት ነው። ይህም በተፈጥሮ ወይም ከወሊድ በኋላ ሊከሰት ይችላል::

## የቃላት ፍቺ

**መብት** - ሰዎች ያላቸውን የሚጠቀሙበትና በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ነው።

**ሰብአዊ መብቶች** - በሰብአዊነታቸው ብቻ ለሁሉም የሰው ልጆች የተሰጡ ናቸው፡፡

**አካላዊ ጉዳት** - የአንድን ሰው እንቅስቃሴ አካላዊ ችሎታ ጥንካሬንና ፍጥንትን የሚጎዳ የረጅም ጊዜ ክስተት ነው.፡፡

**አክብሮት** - ለራስ እና ለሌሎች ሰዎች የሚንሰጠው ክብር ነው፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## ክፍል I. ትክክለኛውን ዐረፍተ ነገር እውነት ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሐሰት ብለህ/ሽ መልስ/ሽ፡፡

1. መብት ማለት አንድ ሰው በሞራልም ሆነ በህግ ያለውና ሊጠቀመው የሚችል ነው።
2. መብትና ግዴታዎች አብረው ይሄዳሉ።
3. ልጆች ከመብታቸው ጎን ለጎን ግዴታዎችም አሏቸው.
4. ማንኛውም ሰው የመናገር መብት አለው።
5. ሁሉም ሰው በተፈጥሮ እኩል መብት አለው።

## ክፍል II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከቀረቡት አማራጮች ምረጥ/ጭ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ፍቅር እና እንክብካቤ　　ሐ. የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ

   ለ. ስድብ እና መድልዎ　　መ. የእኩልነት መብቶቻቸውን ማክበር

2. ____________ የሰው ልጅ ተፍጥሮአዊ ክብር እንዳለው እውቅና መስጠት ነው።

   ሀ. ሰብአዊ ክብር　　ሐ. የአካል ጉዳተኞች መብት

   ለ. የሴቶች መብት　　መ. የህጻናት መብት

3. ከሚከተሉት የሴቶችን መሰረታዊ መብቶች እና ክብርን የሚነካ ተግባር የትኛው ነው?

   ሀ. ጋብቻ　　ሐ. ሰቶች የወንዶችን ስራ መስራት

   ለ. ማህበራዊ ኑሮ　　መ. የሴት ልጅ ግርዛት

4. ከሚከተሉት አካል ጉዳተኝነትን ሊያስከትል የማይችል የትኛው ነው?

ሀ. በሽታ

ለ. የምግብ እጥረት

ሐ. ግጭት እና ጦርነት

መ. ከአካል ጉዳተኛ ልጆች ጋር መጫወት

5. ከሚከተሉት ውስጥ የሴቶች መብት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መሬት የማግኘት መብት

ለ. መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት

ሐ. ሃብት የማፍራት መብት

መ. በሌሎች ላይ የበላይነትን ማሳየት

## ክፍል III. ባዶ ቦታዎችን በትክክለኛ ሐረግ ሙላ/ይ

1. አንድ ሰው በተፈጥሮ ያገኘውንና በህጋዊ መንገድ ሊጠበቅለት የሚገባው________________________ ነው።

2. አንድ ሰው መብቱን ለመጠቀም መወጣት ያለበት ___________ ይባላል።

## ክፍል IV. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው–አጭር መልስ ስጥ/ጭ።

1. አካል ጉዳተኞች ከማህበረሰቡ ምን አይነት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል?

2. በትምህርት ቤትህ/ሽ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ካሉ ምን አይነት ድጋፍ ማግኘት አለባቸው?

# ምዕራፍ 3

# ሰላም

## መግቢያ

በምዕራፍ ሁለት ስለ ሰብአዊ መብት ተምረሃል/ሻል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሰላም ምንነት የሰላም አስፈላጊነትንና ሰላምን ማረጋገጥ የሚቻልባቸውን መንገዶች እንዲሁም የሰላም እጦት የሚያስከትለውን ጉዳት ትማራለህ/ሽ ።

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:-**

- የሰላምን ምንነት ማብራራት
- ለሰላም አስፈላጊነት ትኩረት መስጠት
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የአፈታት ዘዴዎችን ማድነቅ
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ችሎታን ማሳየት
- የሰላም እጦት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መለየት።

## 3.1. የሰላም ምንነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

- የሰላምን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ

## የግንዛቤ ጥያቄ

- ሰላም ምንድን ነው?

ሰላም በግልም ሆነ በቡድን ከግጭት ነፃ ሆኖ በመተሳሰብና በፍቅር መኖር ነው። እንዲሁም ከፈጣሪና ፍጥረታት ጋር ሰላም መሆን ማለት ነው። ሰላም በፍቅር እና በመተሳሰብ አብሮ መኖር ነው። ማለትም ጥላቻንና ጥቃትን በማስወገድ አብሮ መኖር ማለት ነው።

## ተግበር 3.1

1. 1. ሰላም የመማር ማስተማር ሂደትን እንዴት ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል?
2. 2. ሰላም ከለሌ ምን ሊፈጠር ይችላል?

### ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ ካነበብክ/ሽ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

ሀብታሙ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው። አንድ ቀን በክልል ደረጃ በሰላም ጉዳይ ላይ በሚደረገው ውይይት ተገኝቶ ንግግር እንዲያደርግ ተመረጠ። በውይይቱ ከመሳተፉ በፊት ለመምህራንና ለጓደኞቹ ንግግሩን ለማቅረብ ፈለገ። ይህም የንግግር ችሎታውን ለማሻሻል እና ከአድማጮች ግብዐት ለማግኘት ነበር፡፡ የንግግሩ ርዕስም “ሰላም” ነው። ንግግር ሲያደርግ አምስት ሰዎች ንግግሩን ገምግመው አስተያየት እንዲሰጡት ተመድበዋል። የእሱም ንግግር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

“የተከበራችሁ መምህራንና ውድ ጓደኞቼ፣ በሰላም’ ጉዳይ ላይ በክልል ደረጃ በሚደረገው ውድድር ላይ ለመሳተፍ አስበለሁ፡፡ከዚያ በፊት የማቀርበውን ለእናንተ ማቅረብ ፈለኩኝ፡፡.

በአሁኑ ጊዜ “ሰላም” በዓለም ዙሪያ በጣም አንገብጋቢ እየሆነ ነው፡፡. ህይወት

ላላቸው ፍጥረታት በሙሉ አስፈላጊ ነው። ሰላም የውስጥ ደስታንና በጎ ማሰብን ያካትታል። በተጨማሪም ትዕግስት፣ መቻቻል፣ ጽናትንና አጋዥ አመለካከት ውስጣዊ ሰላም ለመፍጠር የሚረዱ ናቸው። ሰላም ከለላ ሰው የሚናገኝ ወይም የሚንጠብቅ ሳይሆን በእኛ በራሳችን ላይ ይመሰረታል፡፡ ለአለም የማህበረሰብ ሰላም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ሰላም በግለሰብ እና በቤተሰብ ደረጃም አስፈላጊ ነው። ሰላም ለአእምሮ ደስታን ይሰጣል::እንዲሁም ደስታን ይሰጣል።

በህይወታችን ውስጥ ሰላም በደፈረሰ ጊዜ ብዙ ችግሮች አጋጥሞን አይተናል። ስለዚህ ሰላምን ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ሰላምን ከሚያደፈርሱ እና ወደ ብጥብጥ ከሚያመሩን ከየትኛውም ድርጊቶች መቆጠብ አለብን። በአጠቃላይ ሰላም በግለሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃ አስፈላጊ ነው።

አመሰግናለሁ!



ምስል 3.1. ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ጸጥታ ላይ ሲወያዩ

## 3.2 የሰላም አስፈላጊነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ  የመማር ብቃቶች፡**

- የሰላምን አስፈላጊነት ትዘረዝራለህ/ሽ;
- የሰላምን አስፈላጊነት ታደንቃለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. የሰላም አስፈላጊነትን ቢያንስ ሶስቱን ዘርዝር/ሪ።
2. የሰላም እጦት በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃ ምን ሊያስከትል እንደሚችል አብራራ/ሪ።

ሰላም የዕድገት መሰረት ነው።እንዲሁም  ለማህበረሰብ መረጋጋትና ለዘላቂ ልማት ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ፣ መቻቻልንና ማህበራዊ ትስስርን ያበረታታል፡፡ ሰላም በግለሰብ፤ በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ደረጃ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማፋጠን ይረዳል::

ሰላም ብዝሃነትን  በማቀፍ እና በሰዎች መካከል መግባባትን በማጠናከር የግለሰቦችንና የማህበረሰብን ህይወት እንዲቀየር ምክንያት ይሆናል፡፡ለሀገር ዕድገትም መሰረት ነው፡፡

## 3.3. ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡**

- ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶችን ትለያለህ/ሽ።

### ተግባር 3.2

1. ሰላም የመማር ማስተማር ሂደትን እንዴት ልደግፍ ይችላል?
2. ሰላም ማህበረሰብን ለማጣመር እንዴት ይረዳል?

### በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን ማጎልበት

#### የግንዛቤ ጥያቄ

በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን የማጎልበቻ መንገዶች ላይ በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሰላም ለቤተሰብም ሆነ ለማህበረሰብ ዕድገት መሰረት በመሆኑ በሁሉም ቦታ ሊጠናከር ይገባል። የህዝቡን ሰላም ለማስጠበቅ ግለሰቦችም ሆነ መንግስት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መተግበር ያለባቸው ሲሆን ማህበራዊ ፍትህ፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ መቻቻል፣ ውይይት፣ ግጭት አፈታት እና መደጋገፍን በመጠቀም ሊሆን ይገባል። ቤተሰብ ለግለሰብ ዕድገትና ደስታ እንዲሁም ለህብረተሰብ ትስስርና ዕድገት መሰረት ነው። ቤተሰብ እንደ ማህበረሰብ አካል በጎ ምግባሮችን ፍቅር፣ አንድነት፣ ርህራሄ፣ ፍትህ፣ መከባበርና ታማኝነት ሰላምን ለማስፈን ወሳኝ ናቸው። እናንተም እንደ ቤተሰብ አባል፣ እነዚህን እሴቶች መለማመድ እናዲሁም ማዳብርና ማክበር አለባችሁ።



ምስል 3.2: የማህበረሰብ ተሳትፎ ሰላምን ለማስፈን ሚና አላው

## የቤተሰብን ሰላም ለማጠናከር የሚረዱ ዘዴዎች:

### 1. መከባበር

የቤተሰብ አባላት በሰላም እና በስምምነት አብረው መኖር አለባቸው፣የቤተሰብ ክብርን የሚነኩትን ነገሮችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡ በቤተሰብ ውስጥ የመከባበር እሴት መኖሩ ቤተሰቡ ደስተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በእናትና አባት፣ በታላቅና በታናሽ መካከል መከባበር ሊኖር ይገባል።



ምስል 3.3፡ የቤተሰብ አባላት እርስ በርስ ሲከባበሩ

## 2. አላስፈላጊ ፉክክርን ማስወገድ

ልጆች መወዳደር ይወዳሉ። ውድድርን ሊትወድ ትችላለህ፡፡ በውድድር ውስጥ የውድድሩን አይነት እና ውጤቱን መጠበቅ አስፈላጊ ነው። አለአስፈላጊ ፉክክርን ማስቀረት ያስፈልጋል፡፡ አላስፈላጊ ፉክክርን ማዕከል ያደረገ ውድድር አለመግባባትና ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል።በቤተሰብና በጓደኞች መካከል አለአስፈላጊ የፉክክር ስሜትን በማስወገድእና አንዱ የቤተሰብ አባል ሌላውን የሚደግፍበት አካባቢ በመፍጠር ታማኝነትንና ፍቅርን ለመገንባት ይረዳል.

## 3. መልካም ግንኙነት

ከቤተሰብህ/ሽ፣ ከጓደኛህ/ሽ እና ከጎረቤቶችህ/ሽ ጋር ሲትጨዋወቱ በተረጋጋ ሁኔታ መሆን አለበት:: ይህ በቤተሰብ ውስጥ ሰላምና መረጋጋትን ለመፍጠር ይረዳል፡፡

## ተግባር 3.3

1. በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ ስልቶችን ዘርዝር/ሪ።
2. ሰላምን በማስፈን ረገድ የወላጆች ሚና ምንድን ነው?

# 3.4. ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፈታት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡**

- የግጭት አፈታት ምንነትን ትገልጻለህ/ሽ;
- ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ዘዴዎችን ትዘረዝራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

- የግጭት አፈታት ማለት ምን ማለት ነው?

ሰላማዊ የግጭት አፈታት ማለት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ መፍታት ነው። እነዚህ ግጭቶች ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ግጭት የመማር ማስተማር ሂደትን የሚያዊክ ሲሆን የሰላም መስፈን ተማሪዎች እና መምህራን በመማር ማስተማር ስራ ላይ እንዳያተኩሩ ያደርጋል። እንደ አንድ ዜጋ የሚከተሉት ክህሎቶች ልኖርህ/ሽ ይገባል፡-

- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት;
- የግጭት መንስኤዎችንና ውጤቶችን መለየት ፤
- በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰብ ውስጥ የመደጋገፍና የመከባበር አስተሳሰብን ማበረታታት፤
- በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ የግጭት መንስኤዎችን የመረዳትና የመከላከል ሃላፊነት አለብህ/ሽ።

ማህብረሰባችን ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል አለው። በማህበረሰባችን ውስጥ በጣም ታዋቂ ከሆኑ የግጭት አፈታት ስልቶች ውስጥ አንዱ ሽምግልና ነው።

## ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ አንብበህ/ሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ

በጉዲና መንደር ውስጥ አንድ ሀይቅ ነበረ። ይህ ሐይቅ ብዙ ዓሣዎችን በውስጡ ይዟል ። የአካባቢው ማህበረሰብም ከሀይቁ ዓሣ በማጥመድ ለምግብነት ይጠቀሙበታል። አንድ ቀን ቢቂላ እና ጉደታ የሚባሉ የአከባቢው ነዋሪ ወጣቶች ዓሣ ለማጥመድ ወደ ሀይቁ ሄዱ። ሁለቱም በሐይቁ ዳርቻ ተቀምጠው ዓሳ ለማጥመድ ይጠባበቁ ነበር። እየተጠባበቁ ሳሉ ድንገት አንድ ትልቅ ዓሳ አዩ እና ቢቂላ ቀድሞ ያዘው። በዓሣው ላይ በቢቂላ እና ጉደታ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ። በሁለቱ ወጣቶች መካከል ትልቅ ጭቅጭቅ ተነሳ።

እየተጨቃጨቁ ወደ ሰፈር ስሄዱ አንድ ሽማግሌ ዘንድ ደረሱ። ሽማግሌው የጭቅጭቃቸውን መንስኤ ጠየቃቸው። በዓሳው ላይ እንደተጣሉ ነገሯቸው። ሽማግሌው በነገሩ በመገረም እንዴት ዓሣ ለጥል ምክንያት ይሆናል? ዓሳውን እኩል ሁለት ቦታ መካፈል ወይም ደግሞ ሁለት ሆናችሁ አብራችሁ መብላት ትችላላችሁ፡፡ ወዳጆች በዚህ ጉዳይ ላይ መጨቃጨቅ ስህተት ነው ሲል መከራቸው።

ቢቂላ እና ጉደታ የሽማግሌውን ምክር ከሰሙ በኋላ ትክክል እንዳልሆኑ ገባቸው። ሁለቱም ጓደኛሞች በዚህ ዓይነት ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ መጋጨት ትክክል አለመሆኑ ስለገባቸው ተጸጸቱና በመጨረሻም ቢቂላ እና ጉደታ ዓሳውን ጠብሰው ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር በጋራ ለመብላት ወስነው ውሳኔያቸውንም ተግባራዊ አደረጉ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሁለቱ ጓደኛሞች መካከል ጠብ አልነበረም። ቢቂላ እና ጉደታም ጥሩ ጓደኛሞች ሆነው ቀጠሉ።

## ተግባር 3.4

**እላይ ባለው ታሪክ ላይ በመመሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ፡፡**

1. ቢቂላ እና ጉደታ በመጨረሻ ምን ዓይነት ውሳኔ ላይ ደረሱ?
2. በቢቂላ እና በጉደታ መካከል የተፈጠረው ግጭት መንስኤው ምን ነበር?
3. በዓሣው ምክንያት የተነሳውን አለመግባባት እንዴት ፈቱ?
4. በዚህ ታሪክ ውስጥ የተገለጹት የሞራል እሴቶች ምንድን ናቸው?

## ሽምግልና

### የግንዛቤ ጥያቄ

- ሽምግልና ምንድን ነው?

ማህበረሰባችን የእርስ በርስ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ሽምግልና ነው፡፡ ሽምግልና አንዱ የእርቅ ማውረጃ መንገድ ሲሆን የሀገር ሽማግሌዎችና የዕድሜ ባለጸጎች እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች እርቅ የማውረድ ሂደት ውስጥ የራሳቸውን ሚና የሚጫወቱበት የሰላም ግንባታ ዘዴ ነው፡፡

በእርቁ ላይ የሚሳተፉት ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች ግጭቶችን የመፍታት አቅም እንዳላቸውም በማህበረሰቡ ይታመናል፡፡ ሹማግሌዎቹ የሚመረጡት ግጭት በመካከላቸው በተፈጠረው በሁለቱ አካላት ነው፡፡ አለመግባባቶችን በሽምግልና የመፈታት ሂደት የማህበረሰቡን ባህል መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ ለተጎጂው አካል ፍትህን ለመመለስና ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ሽምግልና፣ የሀገር ሽማግሌ፣የእርቅ ሽማግሌ እና በመሳሰሉት ስሞችም ይጠራል፡፡



ምስል 3.4: ግጭቶችን በሽምግልና ሂደት መፍታት

## ተግባር 3.5

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ.**

1. በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሽማግሌዎች ሚና ምንድን ነው?
2. ግጭቶችን በሰላም የመፍታት ሂደት ውስጥ ሽማግሌዎች የሚመረጡት በማን ነው?
3. በአካባቢህ በሽምግልና በማገልገል የሚታወቁትን አምስት ሰዎች ዘርዝር/ሪ።
4. በአካባቢያችሁ ግጭቶች እንዴት ይፈታሉ?
5. ሰላምን ለማስጠበቅ በትምህርት ቤት እና በክፍል ውስጥ ማድረግ ያለብህን/ሽን ነገሮች ጻፍ/ፊ።

# 3.5. የሰላም እጦት የሚያስከትለው ጉዳት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

✍ የሰላም እጦት የሚያስከትለውን ጉዳት ትዘረዝራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

- ግጭት ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትላል?

የሰላም እጦት ለአንድ ሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጠንቅ ነው። ግጭት ብዙ ችግሮችን ያስከትላል። ለምሳሌ የአካል ጉዳት፣ ሞት፣የሰዎች መፈናቀልን ፣ሕጻናት በጦርነት ውስጥ መሳተፍንና የበሽታ መስፋፋት እንዲሁም የግብርና ምርት እና ኢንዱስትሪ፣ ንግድና መሠረተ ልማትንም ይጎዳል። በተጨማሪም ማህበራዊ ችግሮችን፣ የአካባቢ ጉዳት፣ ወታደራዊ ወጪ፣ በትምህርት ቤቶችና በቤተሰቦች ላይ የሚደርሰው ጥቃት የሰላም እጦት ውጤቶች ናቸው።

# ማጠቃለያ

ሰላም ከግጭት ነጻ መሆን እና በግለሰቦችም ሆነ በቡድን መካከል ከምከሰት ግጭት ነፃ መሆን ነው። ሰላም ለሀገርና ለግለሰብ ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ነው። የማህበረሰቡን ሰላም ለማስጠበቅ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል።ሰላም በግለሰቦች ወይም በቡድን መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት ይረዳል። ሰላም በሌለበት ሀገር በማህበራዊም ሆነ በኢኮኖሚ ልታድግ አትችልም።

## የቃላት ፍቺ

- **ሰላም** - ከግጭት እና ከጥቃት ነፃ መሆን ነው።
- **ግጭት** - በሁለት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል አለመግባባት መኖሩን የሚያመላክት ነው፡፡
- **አድልዎ** - ኢፍትሃዊ ድርጊት በመፈጸም አንድን ሰው በመጉዳት ለላውን መጥቀም ማለት ነው።
- **እኩልነት** -ጥቅሞችንና ግዴታዎችን በመጋራት በፍትሃዊ ሂደት ሰዎችን ማስተናገድ።

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡** ትክክል የሆነውን ዓረፍተ ነገር "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ።

1. ሰላምን ማስፈን የመንግስት ኃላፊነት ብቻ ነው።
2. ማንኛውም ሰው የማህበረሰቡን ሰላም የማስጠበቅ ሃላፊነት አለበት።
3. ሰላምን ማስፈን ህፃናት እና ወጣቶች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዳል።
4. 4. የሰብአዊ መብቶች መከበርና መቻቻል በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ትልቅ ድርሻ አሏቸው፡፡

**ክፍል II፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከቀረቡት አማራጮች ምረጥ/ጪ**

1. ሰላም የሚያስፈልገው ለማን ነው?

   ሀ. ለግለሰብ　　　　ሐ. ለማህበረሰብ

   ለ. ለቤተሰብ　　　　መ. ለሁሉም

2. ግጭትን የመፍታት ኃላፊነት የማን ነው?

   ሀ.የሽማግሌዎች　　　　ሐ. የቀሳውስት

   ለ. የመንግስት　　　　መ. የሁሉም የህብረተሰብ አባላት

3. ከሚከተሉት ስልቶች የቤተሰብ ሰላምን ለማረጋገጥ ጠቃሚ የትኛው ነው?

   ሀ. አላስፈላጊ ውድድር　　　　ሐ. አላስፈላጊ ንግግር

   ለ. መደጋገፍን ማስወገድ　　　　መ. መከባበርን ማበረታታት

4. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በደህንነት ማጣት ምክንያት ይከሰታል

   ሀ. የኢኮኖሚ ዕድገት

   ለ. ማህበራዊ ኑሮ መረጋጋት

   ሐ. የህዝብ መፈናቀል

   መ. የግብርና ምርታማነትን ጨምሯል።

**ክፍል III፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ**

1. መሰረታዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
2. በቤተሰብ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ምን ምን ዘዴዎች ተግባራዊ ይሆናሉ?

# ምዕራፍ 4

# በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያስፈልግ መልካም ሥነ-ምግባር

## መግቢያ

በምዕራፍ 3 ውስጥ ስለ ሰላም ተምረሃል/ሻል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የሥነ-ምግባርን ፍቺና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ትማራለህ/ሽ፡፡ እንዲሁም የእረፍት ጊዜህን/ሽን በአግባቡ መጠቀምና በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት ትለያለህ/ሽ፡፡ በተጨማሪም ለመንገድ ትራፊክ የሚያስፈልጉ ደንቦችንና የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ትማራለህ/ሽ፡፡

### የምዕራፉ የመማር ውጤቶች ፡-

- የመልካም ሥነ-ምግባርን ፍቺ መግለጽ፣
- ሥነ-ምግባር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት መግለጽ፣
- የእረፍት ጊዜን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ መግለጽ፣
- በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት መለየት፣
- ለመንገድ ትራፊክ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችንና መመሪያዎችን መለየት፣
- በማህበራዊ አገልግሎቶች ውስጥ አስፈላጊ ለሆኑ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች ቦታ መስጠት.

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

- መልካም ተግባርና አስጸያፊ ተግባራት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው ?

## 4.1. የመልካም ሥነ-ምግባር ምንነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ :-

- የመልካም ሥነ-ምግባርን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ፤
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ትዘረዝራለህ/ሽ.

ሥነ-ምግባር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መልካምና አስጸያፊ የሆኑ ተግባራትን የሚያመላክት ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ተግባር መልካም ወይም ጸያፍ መሆኑ በማህበረሰብ ውስጥ የሚለካበት ነው፡፡ መልካም ተግባራት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው እሴቶች የሚንጸባረቁበት ሲሆን ጸያፍ ተግባራት ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውና የሚጠሉ ናቸው፡፡አንድ ሰው በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያለውን ተግባር የሚፈጽም ከሆነ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ሰው ነው ይባላል፡፡በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ተግባር የፈጸመ ሰው ከሆነ ደግሞ ሥነ-ምግባር የሌለው ነው ይባላል፡፡

### ተግባር 4.1

1. ሥነ-ምግባር ምንድን ነው ?
2. በመኖሪያ ቤትና በትምህርትቤታችሁ ምን ዓይነት ተግባራትን እንዲታከናውን ይጠበቅብሃል/ሻል?
3. በትምህርት ቤት ውስጥ መልካም ሥነ-ምግባር ያለህ/ሽ መሆኑ ምን ይጠቅመሃል/ሻል?
4. ወላጆች ልጆቻቸው መልካም ባህሪይ እንዲኖራቸው በማድረግ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና ወላጆችህን/ሽን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አብራራ/ሪ፡፡



ሥዕል 4.1: ተማሪዎች መልካም ሥነ-ምግባርን የተላበሱ መሆን አለባቸው

ልጆች መልካም ሥነ-ምግባር እንዲኖራቸው አድርጎ ማሳደግ የወላጆችና የአሳዳጊዎች ሀላፊነት ነው፡፡ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችም ተማሪዎች መልካም ሥነ-ምግባር እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር ከወላጆች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በማህበረሰቡ ውስጥ መልካም ስነ ምግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም መልካም ሥነምግባር ማሳየት አለባቸው፡፡

## ለምሳሌ፣

- የመማሪያ ክፍል ሥነ-ሥርዓትና የትምህርት ቤት ደንቦችን ማክበር፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ የሚገኙ የትምህርር ቤቱ ንብረቶችን እንዳይበላሹ መጠበቅና መንከባከብ፤
- የመማሪያ ክፍሎችንና የትምህርት ቤቱን ቅጥር ግቢ ንጽህና መጠበቅ፤
- የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ማክበር፤
- ሌብነትን ማውገዝና ማጋለጥ፤
- ሰዎችን ማክበር፤
- እውነትን መናገርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**በመማሪያ ክፍላችን ውስጥ፡-**

- አንድነት(ቡድን) አለን;
- ቀናዎች ነን፤
- እንከባበራለን፤
- ታማኞች ነን፤
- እንደጋገፋለን፤
- እንደማመጣለን፤
- ጠንክረን እንማራለን
- የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን፤
- ሁላችንም እናስፈልጋለን፡፡

## የትምህርት ቤት ደንቦችን የሚያሳይ ሳጥን

## ተግባር 4.2

ከዚህ በታች የቀረበውን ሠንጠረዥ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ የተዘረዘሩትን ተግባራት/ባህርያት መልካም ተግባራት ወይም ጸያፍ ተግባራት መሆናቸውን '√' ምልክት በማድረግ አመልክት/ቺ፡፡

| ተ.ቁ | ተግባራት/ባህሪያት | መልካም ተግባር | ጸያፍ ተግባር |
|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርት ቤቱንና የመማሪያ ክፍልን ደንብ ማክበር | | |
| 2 | በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ማየት የተሳናቸው ተማሪዎችን መርዳት | | |
| 3 | ከሰዎች ጋር አለመግባባት | | |
| 4 | ወላጆችንና አዛውንቶችን ማክበር | | |
| 5 | በአካባቢ እንክብካቤ ሥራ ላይ መሳተፍ | | |
| 6 | ምስጢር መጠበቅ | | |
| 7 | እውነት መናገር | | |
| 8 | ሐሰት መናገር | | |
| 9 | መስረቅ | | |

## 4.2. በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የመልካም ሥነ-ምግባር አስፈላጊነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ:-

- መልካም ሥነ-ምግባር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ትለያለህ/ሽ፤
- መልካም ተግባራት የሚገለጹባቸውን መንገዶች ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡

በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ መልካም ሥነ-ምግባር አስፈላጊ ነው፡፡

ሥነ-ምግባርን የመጎናጸፍ ጥቅሞች :-

- በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትና ክብር ያስገኛል፣
- ሰዎችን በእኩል ለማየት ይረደናል፣
- በትምህርትና በስራ ስኬታማ ለመሆን፣
- ጭንቀትን ለማስወገድና
- የማህበረሰቡን ኖሮ ለማሻሻል ይረዳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መልካም ሥነ-ምግባር መጎናጸፍ ከሌብነት፣ ከዝርፊያ፣ ከማታለልና ሌሎች ሰዎችን ከመጉዳት እንዲንቆጠብ ያደርጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በማህበረሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ በሀገር ዕድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ካለው ሙስና እራስን ለመጠበቅ፣ ነውርን ማወቅና ታማኝ መሆን ወሳኝ ናቸው፡፡ በትምህርት በኩልም መልካም ሥነ-ምግባርን መጎናጸፍ፣ በራስ የመተማመንና በአቋም መጽናትን ማጠናከር በትምህርት ዘርፍ ውጤታማ ያደርጋል፡፡



ሥዕል 4.2: ተማሪዎች በማህበራዊ ሥራዎች ላይ ሲሳተፉ

## ተግባር 4.3

ከዚህ በታች የቀረበውን ሠንጠረዥ በመመልከት በማህበራዊ ህይወት ውስጥ መልካም የሆኑና ጸያፍ የሆኑ ተግባራት ተዘርዝረዋል፡፡ ስለዚህ የትኛው ተግባር መልካም እንደሆነና ጸያፍ ተግባር እንደሆነ '√' ምልክት በማድረግ አመልክት/ቺ፡፡

| ተ.ቁ | ተግባራት/ባህርያት | መልካም ተግባር | ጸያፍ ተግባር |
|---|---|---|---|
| 1 | ሐዊ የእርስዋን እርሳስ ከሚልኬሶ ጋር በጋራ ይጠቀማሉ፡፡ | | |
| 2 | አብዲ ለወላጆቹና ለጎረቤቶቹ አክብሮት አለው፡፡ | | |
| 3 | ቦና ለሌንሳ ጠፍቶባት የነበረውን መጽሐፏን አግኝቶ ሰጣት፡፡ | | |
| 4 | ጫልቱ ያለተራዋ ከጓደኞችዋ ጋር መጫወት ትፈልጋለች፡፡ | | |
| 5 | ደራራ ከብስክሌት ላይ ሲወድቅ ኦላና ድጋፍ አደረገለት፡፡ | | |
| 6 | ኢፍቱ ኦብሴን ሥራ ረዳቻት፡፡ | | |

## 4.3. የዕረፍት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የዕረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ታስረዳለህ/ሽ፤
- የዕረፍት ጊዜን በአግባቡ የመጠቀምን አስፈላጊነት ትለያለህ/ሽ፡፡

የዕረፍት ጊዜ የሚባለው ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ነጻ በመሆን እረፍት የሚደረግበት ነው፡፡ ይህ ጊዜ በሥራ የደከመውን አእምሮአችንን ለማደስና ሌሎች ሥራዎችን ለማከናወን አስፈላጊ ጊዜ ነው፡፡

የዕረፍት ጊዜያችንን የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫወት፣ የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍና ታሪካዊ ሥፍራዎችን በመጎብኘት ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሁላችሁም የዕረፍት ጊዜያችሁን በአግባቡ መጠቀም ይገባችኋል፡፡

### የሌሊት ወፍ ትረካ



በዱሮ ጊዜ የረሃብ ዘመን የነበረበት ዓመት ነበር ይባላል፡፡ በዚያን ዓመት ረሃብ ስለጸና ወፎች የሚበሉት አጥተው ተቸገሩ፡፡ከዚህ በኋላ ሁሉም ወፎች ከሰው ዘንድ በመሄድ የሚበላ ነገር ለመበደር ወሰኑ፡፡ በዚሁ መሰረት ከአንድ ባለሃብት ዘንድ በመሄድ የምንበላው አጥተናልና ዝናብ በዘነበ ጊዜ እርሻችንን

አርሰን ዘር በመዝራት ምርት ስናገኝ ብድርህን እንከፍላለን ፡፡ ይህን የረሃብ ዘመን የሚያሳልፍልንን ብድር አበድረን አሉት፡፡ ባለሃብቱም ክረምት ሲገባ ሁላችሁም የተበደራችሁትን ልትመልሱልኝ ይገባል በማለት የሚፈልጉትን ሰጣቸው፡፡ ወፎቹም እሺ እንመልስልሃለን ብለው ቃል በመግባት ወደ መጡበት ተመለሱ፡፡

ከዚህ በኋላ የረሃቡ ዘመን አልፎ ዝናብ ዘነበ፡፡ ወፎቹም መሬታቸውን አርሰው በመዝራት ከፍተኛ ምርት አመረቱ ይባላል፡፡ ከዚህ በኋላ ወፎቹ በሙሉ የተበደሩትን እህል ለባለሃብቱ መልሰው የተቀረውን ለራሳቸው አስቀመጡ፡፡ በዚህን ጊዜ የሌሊት ወፍ "እኔ በዝናብና በጭቃ አላርስም" እያለች ስትዝናና የዝናብ ወቅት አለፈባት፡፡ በዚህ ምክንያት የሌሊት ወፍ ብቻ የተበደረችውን እህል ሳትከፍል ቀረች፡፡ ባለሃብቱም "ይህች ወፍ የተበደረችውን እህል ለምንድን ነው የማትከፍለኝ?" በማለት ዘወትር ሌሎች ወፎችን ይጠይቃቸዋል፡፡ ባለሃብቱ እጅግ በማዘን የሌሊት ወፍዋን ለመግደል ይዝትባታል፡፡

ከዚህ በኋላ የሌሊት ወፍዋ ሰውየውን ስለምትፈራ ቀን ቀን ፈጽሞ ከቤትዋ መውጣት አቁማ ከዋሻዋ ውስጥ ትውላለች ይባላል፡፡ ሌሊት ሌሊት ብቻዋን በመውጣት የሚበላ ትፈልግ ነበር፡፡ የሌሊት ወፍ የሌሊት ወፍ ተብላ የቀረችውም በዚህ ምክንያት ነው ይባላል፡፡

## ተግባር 4.4

1. ከላይ ከቀረበው ተረት ምን ተረዳህ/ሽ?
2. በዚህ ተረት መሰረት ከሌሊት ወፍና ከሌሎች ወፎች ጊዜውን በአግባቡ የተጠቀመው ማነው? ለምን?
3. ሰርቶ በማረፍና ያለ ሥራ በመቀመጥ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ተወያዩ.

## 4.4 በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ  የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ተግባራት ትለያለህ/ሽ፤
- ተቀባይነት የሌላቸውን ተግባር በመፈጸም ሊከሰቱ  የሚችሉትን ጉዳቶች ትገልጻለህ/ሽ፡፡

ማህበራዊ ኑሮ ማለት አንድ ማህበረሰብ በኑሮው ሂደት ውስጥ የሚያከናውናቸው የተለያዩ ተግባራት ናቸው፡፡  በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት አሉ፡፡ ተቀባይነት ያላቸው ተግባራት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚበረታቱ ሲሆኑ ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት ደግሞ  የሚነቀፉ ተግባራት ናቸው፡፡

ተቀባይነት ካላቸው ተግባራት መካከል የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የአባትና እናትን ምክር ማዳመጥ፤
- ቤተሰብን መርዳት፤
- ተራን ጠብቆ ከጓደኛ ጋር መጫወት፤
- አዛውንቶችን ማክበር፤
- የግል ንጽሕናን መጠበቅ፤
- የቤት ሥራን በአግባቡና በትኩረት መስራት፤
- በሥራ ላይ ጠንካራ አቋም መያዝ፤
- መምህራንን ማክበር፤
- ወንድማማችነትን፣ ጉርብትናንና  ወዳጅነትን  ማጠናከር፤
- ማህበረሰቡንና አገርን መውደድ.

ተቀባይነት ከሌላቸው ተግባራት መካከል  የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኩረጃ፣
- የሌላ ተማሪ የሆነን ንብረት መስረቅ፣.
- የትምህርት ቤትን ንብረት ማበላሸትና  ማባከን፣
- ያለ በቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት፣
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መረበሽ፡፡

## ተግባር 4.5

1. በአካባቢህ/ሽ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ተግባራት አምስት አምስት ተግባራት ወላጆቻችህን/ሽን ጠይቀህ/ሽ በመጻፍ ለክፍል ለጓደኞችህ/ሽ አቅርብ/ቢ፡፡ .

2. ከታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ከተዘረዘሩት ተግባራት መካከል ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ተግባራት “✓” በማድረግ አመልክት/ቺ፡፡

| ተ.ቁ | ተግባር | ተቀባይነት ያለው | ተቀባይነት የሌለው |
|---|---|---|---|
| 1 | ወላጆችን፣ መምህራንንና ሽማግሌዎችን/ አዛውንቶችን ማክበር | ✓ | |
| 2 | ማርፈድ | | ✓ |
| 3 | በፕሮግራም አለማጥናት | | |
| 4 | ባለን አቅም የተቸገረውን ሰው መርዳት | | |
| 5 | በፈተና ወቅት መኮራረጅ | | |
| 6 | ለታላላቆቻችን መታዘዝ | | |
| 7 | ጊዜን በአግባቡ መጠቀም | | |
| 8 | ሰዎችን ማታለልና መዋሸት | | |
| 9 | ከጓደኛ ጋር መጣላት | | |
| 10 | የትምህርት ቤትን ንብረት ማበላሸትና ማጥፋት | | |

በቤተሰብ መካከል የሚከናወኑ ሆነው ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ተግባራት  በቤተሰብ መካከል ማከናወን ተቀባይነት ያለው ሲሆን አለማከናወን ደግሞ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

- ከምግብ በፊትና በኋላ እጅን መታጠብ፤
- ተረጋግቶ መመገብ፤
- ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች መጠንቀቅ፤
- ከጓደኛ ጋር ለመጫወት ከመሄድ በፊት ወላጅን ማስፈቀድ፤
- ለረጅም ጊዜ የቆየን ምግብ አለመመገብ፤
- የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችን አለመነካካትና በቁሳቁሶቹ አለመጫወት፤
- እሳት ካለበት ቦታ  መራቅ፤
- ስለት ያላቸውን ቁሶች  ማለትም  ምላጭ፣ መርፌ፣ መጥረቢያ እና ሌሎችንም አለመነካካት፡፡



ሥዕል  4.3: ያለ በቂ ግንዛቤ ጉዳት የሚደርሱ ቁሶችን አለመነካካት

**በአካባቢያችን የሚከናወኑ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት**

ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት ማከናወን ተቀባይነት ያለው ሲሆን አለማከናወን ደግሞ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

- ሕግን ማክበር፤
- ምክርን ማዳመጥና መልካም ሥነ-ምግባርን መላበስ፤
- መርዛማና ጉዳት ከሚያስከትሉ ነገሮች መጠንቀቅ፤
- የማናውቃቸውን ተክሎች ፍራፍሬና አትክልቶችን አለመብላት፤
- የሞላ ወንዝ ወይም ውሃ አለመጠጋትና አለመግባት፤
- በመንገድ ላይ ያየናቸውን የዱር አራዊቶችን አለመነካካት፤
- የኩሬ ውሃ ባለበትና በጨቀየ ስፍራ አለመጫወት፤
- በሰው ጆሮ ላይ አለመጮህ፤
- ስለት ባላቸው ነገሮች ጆሮን አለማከክ ናቸው፡፡

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ተግባራትን በመንገድ ላይ ማከናወን ተቀባይነት ያለው ሲሆን አለመተግበር ደግሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

- ዘወትር እያስተዋሉና ከልብ እያዳመጡ መሄድ፤
- በመኪና ወይንም ተሽከርካሪ መንገድ ላይ ፊጽሞ አለመጫወት፤
- መንገድ ስንሄድ የእግረኛ መሄጃን መጠቀም፤
- መንገድ ከማቋረጣችን በፊት ግራና ቀኛችንን ማየት፤
- ወንዝ ለመሻገር ድልድይ መጠቀም፤
- መንገድ ለማቋረጥ የዜብራን ምልክት መጠቀም ናቸው፡፡

**በትምህርት ቤት የሚከናወኑ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት**

ከዚህ በታች የቀረቡ ተግባራትን በትምህርት ቤት ማከናወን ተቀባይነት

ያለው ሲሆን አለመተግበር ደግሞ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

- የትምህርት ቤት ደንቦችን ማክበር፤
- ሰዓት ማክበር፤
- በንግግራችን ውስጥ መልካም ቃላትን መጠቀም፤
- ተገቢውን የአለባበስ ሥረዓት መከተል፤
- የትምህርት ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ፤
- ለሌሎች ተማሪዎች ጥንቃቄ ማድረግ፤
- በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን አለመወራወር፤
- በጨዋታ ወቅት ተራን ጠብቆ መጫወት፤
- ትዕግስተኛ መሆንና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## አብሳና ሶሬቲ

አብሳና ሶሬቲ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሁለቱ ልጆች እህትና ወንድም ሲሆኑ ዘወትር ጥርሳቸውን ፍቀው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ አብሳ ጥርሱን ለመፋቅ ሳሙና መጠቀም ይወዳል፡፡ ሶሬቲ ደግሞ የእንጨት መፋቂያ መጠቀም ትወዳለች፡፡ ሁለቱም የየራሳቸው መፋቂያ አላቸው፡፡ የሌላ ሰው የጥርስ መፋቂያ በጋራ አይጠቀሙም፡፡ እርስ በእርስም መፋቂያቸውን ተቀያይረው አይጠቀሙም፡፡ ሁለቱም የሚወዱትን የጥርስ መፋቂያ ለየግላቸው ይጠቀማሉ፡፡ ስለዚህ አብሳና ሶሬቲ ንጹህና ጤናማ የሆነ ጥርስ አላቸው፡፡



ሥዕል 4.4: የግል ንጽህና በአግባቡ መጠበቅ

## ተግባር 4.6

1. ኦብሳና ሶሬቲ ምን ዓይነት የጥርስ መፋቂያ ይጠቀማሉ?
2. ኦብሳና ሶሬቲ ጥርሳቸውን ዘወትር የሚያጸዱት ለምንድን ነው?
3. የጥርሳቸውን መፋቂያ ከሌሎች ሰዎች ጋር የማይጠቀሙት ለምንድን ነው?

# 4.5. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ምንነት ትናገራለህ/ሽ፤
- ልንከተላቸው የሚገቡ የመንገድ ትራፊክ ደንቦችን ትለያለህ/ሽ፡፡

## የግንዛቤ ጥያቄ

- የመንገድ ትራፊክ ደንቦችን ባለማክበር የሚከሰቱ አደጋዎች ምን ምንድን ናቸው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?



ሥዕል 4.5. የመንገድ ትራፊክ ደንቦችን ማክበር

የመንገድ ትራፊክ የሚባለው ተሽከርካሪዎች በብዛት የሚንቀሳቀሱበት መንገድ ነው፡፡ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የሚባለው ደግሞ በሕይወትና በንብረት ላይ ሊደርስ ከሚችል አደጋ ለመዳን ሲባል የሚደረግ ጥንቃቄ ነው፡፡ ጥንቃቄ

ሳያደርጉ በመኪና መንገድ ላይ መጓዝ ክልክል ነው፡፡ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዓላማም ሊከሰት የሚችልን የመኪና ጉዳትና አደጋ ማለትም ህይወት ማጣት፣ የአካል ጉዳትንና የንብረት ውድመትን ለመቀነስ ነው፡፡



ሥዕል 4.6. አሽከርካሪዎች በጥንቃቄ ማሽከርከር አለባቸው

ተግባራዊ ሊደረጉ ከሚገባቸው የመንገድ ትራፊክ ደንቦች መካከል ጥቂቶቹ፡

- በመኪና መንገድ ላይ አለመጫወት ወይም አለመሯሯጥ፤
- መንገድ ከማቋረጥ በፊት ግራና ቀኛችንን ማየት፤
- መንገድ ስናቋርጥ የዜብራ ምልክትን መስመሩን ብቻ መጠቀም፤
- መንገድ ስንሄድ በእግረኛ መንገድ ብቻ መጠቀም፤
- ከተፈቀደው ቦታ በስተቀር በሌላ መንገድ ለማቋረጥ አለመሞከር፤
- መንገድ ሲናቋርጥ ሰዎችን አለማናገርና በስልክ አለመነጋገር፤
- አደባባይ ላይ ፈጽሞ መንገድ ለማቋረጥ አለመሞከር፤
- ብስክሌት ስንነዳ የብስክሌቱን ደህንነት ማረጋገጥ፤
- መኪና ስንሳፈርም ሆነ ስንወርድ እስኪቆም ድረስ መጠንቀቅ፡፡

## ተግባር 4.7

1. የመኪና መንገድ ከማቋረጣችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?
2. .መኪና ስንሳፈርና ስንወርድ ምን ማድረግ አለብን?

# 4.6. በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚፈለጉ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ:-

- በማህበራዊ አገልግሎቶች ውስጥ የሚፈለጉ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆችን ትለያለህ/ሽ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

1. በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ ሥራ ላይ መዋል የሚችሉት የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች የትኞቹ ናቸው?
2. በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ ያሉ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች ጠቀሜታዎች ምን ምንድን ናቸው?



ሥዕል 4.7: ድጋፍ የሚሹ አዛውንቶች እና አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ

በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ እነዚህም በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፣ ሰብዓዊ መብት ማክበር፣ እውነተኛነት፣ ምስጢር መጠበቅ፣ ለሰዎች ማሰብ፣ ፍቃደኛ መሆን፣ እራስን መሰጠትና በብቃት ማህበረሰቡን ማገልገል ናቸው፡፡ በእነዚህ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች ላይ ያልተደገፈ አገልግሎት ተልዕኮው የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ .

ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚባሉት ባለን ጉልበትና እውቀት እንዲሁም አቅም የተቸገረን ሰው መርዳት፤ አካባቢን ማጽዳትና ማስዋብ፤ ለአዛውንቶች ቅድሚያ መስጠት፤ የመማሪያ ክፍልን ማጽዳትና በትምህርት ቤት ክበባት ውስጥ መሳተፍ፤ በልግስና ተግባራት ላይ መሳተፍ እንዲሁም የትምህርት ቤቱን ንብረት ከጥፋትና ውድመት መጠበቅ ናቸው፡፡

| |
|---|
| እኔ ተማሪ ______________________ መሆን ያለብኝን ለመሆን በታማኝነት ለራሴ ቃል እገባለሁ፡፡ በትምህርት ቤቴ ለመቆየትና ማወቅ ያለብኝን እንዲማር፣ ይህች ዓለም እንደኔ ያሉ ሕጻናት የሚያድጉባት መልካም ምድር እንድትሆን ለማድረግ ቃል እገባለሁ፡፡ ሕልሜን ለማሳካትም መሆን የሚገባኝን ሁሉ መሆን እንዲችል ቃል እገባለሁ፡፡ እንደምሆንም አውቃለሁ፤ ለዚህም ቃል እገባለሁ! |

# ማጠቃለያ

ሥነ ምግባር የመልካምና የመጥፎ ተግባራት መለኪያ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው ተግባራት እንደመኖራቸው ያህል ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራትም አሉ፡፡ ስለዚህ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት መለየትና መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ሕግን ማክበር፣ ጠቃሚ ምክሮችን ማዳመጥና መልካም ሥነ-ምግባርን መላበስ ጤናማ ያደርጋል፡፡ መልካም ባህሪይ መላበስ ከተለያዩ አደጋዎች እንድንድን ሲረዳን ብልሹ ባህሪይ ደግሞ ለተለያዩ አደጋዎች ያጋልጠናል፡፡

## የቃላት ፍቺ

- **መልካም ተግባር:-** በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው .
- **ጸያፍ ተግባር:-** በማሕበረሰቡ ዉስጥ የተከለከሉና ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት.ናቸው፡፡
- **ሥነ-ምግባር :** ሰውኛ ባህሪይ፣ ሰው የሚያስብበት መንገድ፣ ነገሮችን ማመዛዘንና መልካም ተግባራትንና ጸያፍ ተግባራትን በመለየት ማመዛዘን ነው፡፡
- **ትክክለኛነት :-** በሚፈለገው መልካምነት ዓይነት ማሰብ፣ መንቀሳቀስና መተግበር፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## I. ትክክል የሆነውን ዓረፍተ-ነገር እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት ጻፍ/ፊ፡፡

1. መልካም ሥነ-ምግባር ለሰው ልጆች ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊ ነው፡፡
2. ከጸያፍ ተግባራት አንዱ በፈተና ወቅት ከሌላ ተማሪ ለመኮረጅ ወይም ለመገልበጥ መሞከር ነው፡፡
3. ምስጢር መጠበቅ የታማኝነትና የመልካም ባህሪይ መላበስ መስፈርት ነው፡፡
4. የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡

## II. በ"ለ" ስር ከቀረቡ ሐረጎች መካከል በመምረጥ በ "ሀ" ስር ከቀረቡት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መጋለጥ የሌለበት ጉዳይ | ሀ. ተቀባይነት ያላቸው ጉዳዮች |
| 2. የተፈቀዱ ታግባራት | ለ. ተቀባይነት የሌለው ተግባር |
| 3. ያለተራ ለመጫወት መሞከር | ሐ. ምስጢር |
| 4. ተቀባይነት ያለውና የሌለው ባህሪይ መለኪያ | መ. ሥነ-ምግባር |
| 5. ሕጻናት መልካም ሥነ-ምግባር መላበስ የሚጀምሩበት ሥፍራ ሠ.ቤተሰብ | |

## III. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጪ፡፡

1. ከታች ከቀረቡት ውስጥ የመልካም ሥነ-ምግባር ጉድለትን የሚያመላክተው ባህሪይ የትኛው ነው?
   ሀ. የትምህርት ቤትን ሕግና ደንብን ማክበር
   ለ. የመማሪያ ክፍልን ንጽሕና መጠበቅ
   ሐ. የሌሎች ተማሪዎችን ንብረት አለመውሰድ
   መ. ሌሎች ሰዎችን ማስፈራራት

2. ከባልደረቦቻችን ጋር በጋራ ቃል የገባነውን ነገር መጠበቅ---------------- ይባላል፡፡

    ሀ. የቤተሰብ ምስጢር            ሐ. የባልንጀራ ምስጢር

    ለ.የሀገር ምስጢር            መ. የትምህርት ቤት ምስጢር

3. ከታች ከቀረቡት መካከል በዕረፍት ጊዜህ/ሽ ልትሳተፍበት የማይገባው የትኛው ነው ?

    ሀ. መጽሐፍ ማንበብ            ሐ.ቤተሰብን መረበሽ

    ለ. መዝናናት            መ. ከጓደኛ ጋር መጫወት

4. መልካም ሥነ-ምግባር እንዳለው ሰው በቤተሰብ ውስጥ የሚጠበቅብህ/ሽ ተግባር ምንድን ነው?

    ሀ. ቤተሰብን ማስደሰት            ሐ. ቤተሰብን ተስፋ ማስቆረጥ

    ለ. ቤተሰብን አለማስደሰት            መ. ቤተሰብን ማስቆጣት

5. ከሌላ ሰው ልንማረው የሚገባው ሥነ-ምግባር ምንድን ነው?

    ሀ. መልካም ተግባር            ሐ. ሥነ-ምግባር አልባነት

    ለ. ደካማ ተግባር            መ. የተሳሳተ ተግባር

## IV. ከታች የቀረበውን ባዶ ቦታ በትክክለኛ መልስ ሙላ/ይ፡፡.

1. ከተማሪዎች የሚጠበቁ ሶስት መልካም ተግባራትን ጻፍ/ፊ፡፡

    ሀ. ________________________________________

    ለ. ________________________________________

    ሐ. ________________________________________

# ምዕራፍ 5

# የመቻቻል ባህል

## መግቢያ

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ስለ መልካም ሥነ-ምግባር ሚና ተምረሃል/ሻል፡፡በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ መቻቻል ባህል ምንነት ፤ የመቻቻል አመልካቾች ፤ የመቻቻል አስፈላጊነት፤ የመቻቻል ባህሪያትና በመቻቻል ሂደት ውስጥ እንቅፋት ስለሚሆኑ ነገሮች ትማራለህ/ሽ፡፡

### የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች :-

- የመቻቻልን ምንነትን መግለጽ
- የመቻቻል አመልካቾችን መለየት
- የመቻቻልን አስፈላጊነትን መዘርዘር
- የመቻቻል ባህሪይን ማንጸባረቅ
- ለመቻቻል ባህል መዳበር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን መለየት

## 5. 1. የመቻቻል ባህል ምንነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የመቻቻል ባህልን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ፤.
- የመከባበርን ባህል በተግባር ታሳያለህ/ሽ፡፡

### የግንዛቤ ጥያቄ

- የመቻቻል ባህል ማለት ምን ማለት ነው?
- የመቻቻል ባህል ተግባራዊ የሚሆነው የት ነው?

መቻቻል ልዩነትን በትዕግስት በመቀበል በሰላም አብሮ መኖር ማለት ነው፡፡ ልዩነቱም በሃሳብ፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት በአመለካከትና በሌሎችም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ልዩነቶቻችንን በማክበርና በመቻቻል እውቅና በመስጠትና በሰላም አብሮ መኖር ይገባል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ በባህልና በእሴት ልዩነት ውስጥ አብሮ በመኖር ረጅም ታሪክ ያላት ናት፡፡ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረ-ሰቦችና ሕዝቦችን አቅፋ የያዘች አገር ናት ፡፡ እነዚህ ሕዝቦች የሚከውኑት የራሳቸው የሆኑ የሚከበሩ በዓላትና የተለያዩ ሥርዓቶችን ይዘው ተቻችለው አብረው ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም የሚፈጠሩ ግጭቶችን የሚፈቱባቸውና ይቅርታ የሚባባሉባቸው የተለያዩ ሥርዓቶችንም አሏቸው፡፡

### ተግባር 5.1

- በመቻቻል ምንነት ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## 5. 2. የመቻቻል ባህል መገለጫዎች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የመቻቻል ባህልና አመለካከቶችን ትለያለህ/ሽ፡፡

### የግንዛቤ ጥያቄ

የመቻቻል ባህል አመልካቾች ምን ምንድን ናቸው?

ከመቻቻል ባህል አመልካቾች መካከል ጥቂቶቹ፡-

- የቋንቋ እኩልነት መብት
- እኩል የመዳኘት መብት
- ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት
- የሃይማኖት እኩልነት፣
- የዜጎች የእኩልነት መብት

የመቻቻል ባህል ያለው ማህበረሰብ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዳለው ይታመናል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ማህበረሰብ የሕዝቦችን ባህልና ቋንቋ መንከባከብና ያለውን ልዩነት በማክበር በእኩልነት አብሮ ይኖራል፡፡በተጨማሪም የመቻቻል ባህል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አመለካከቶችን ያካትታል፡፡

- እውቅና መሰጣጣት
- ተቀባይነት ያለው መሆን
- አክብሮት
- አንዱ የሌላውን ሃሳብ መረዳት ናቸው፡፡



ስዕል 5.1. ልዩነቶቻችን በማክበር በእኩልነት አብሮ መኖር

## ተግባር 5.2

ከዚህ በታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡

1. ከቀረቡት መካከል የመቻቻል ባህል የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ከሰው መራቅ ሐ. ሰው ማክበር

   ለ. የሌሎችን ባህል መናቅ መ. ሰውን መሳደብ

2. ከዚህ በታች ከቀረቡት መካከል የመቻቻል ባህል የሌለው ባህሪይ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. የቋንቋ ጥላቻ ሐ. የፖለቲካ አመለካከት ነጻነትን ማክበር

   ለ. ሰዎችን ማክበር መ. የሃይማኖት እኩልነትና ነጻነትን ማክበር

3. ከዚህ በታች ከቀረቡት መካከል የተለየው የትኛው ነው?

ሀ.ፍትህ ማጣት
ሐ. ሰዎችን መርዳት
ለ. ሰዎችን ማግለል
መ. አካል ማጉደል

## 5.3. የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት ትገልጽለህ/ሽ፡፡

### የማንዛቤ ጥያቄ

- የመቻቻል ባህል ለምን ያስፈልጋል?

የመቻቻል ባህል ከዚህ በታች የተገለጹ ጠቀሜታዎች አሉት:-

- መቻቻል ሰላም ለመፍጠርና ግጭትን ለመቀነስ ይረዳል፡፡
- መቻቻል መረጋጋትን ተስፋና ሰላም በቀጣይነት እንዲኖር ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጎረቤቶቻቸው፣ ከትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ከመምህራኖቻቸው ጋር አብረው እንዲኖሩ ይረዳቸዋል፡፡
- ሰላም የሕብረተሰቡን ሰላምና ፍቅር በማጎልበት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡
- የባህል ብዝሃነት ተቀባይነት ማግኘትን ያጠናክራል፡፡

### ተግባር 5.3.

የመቻቻል ባህል ለምን ያስፈልጋል?

## 5.4. ለመቻቻል ባህል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ለመቻቻል ባህል እንቅፋት የሚሆኑትን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- የመቻቻል ባህሪይን ታንጸባርቃለህ/ሽ፡፡

### የግንዛቤ ጥያቄ

- የመቻቻል ባህል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ምን ምንድን ናቸው?

ለመቻቻል ባህል ላለመዳበር እንቅፋት የሚሆኑ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ሰዎች የመቻቻልና መከባበርን ባህል በትምህርት ቤት፣ በማህበረሰቡና በእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ በተጨባጭ ሥራ ላይ ያለማዋል ጉዳይ ነው፡፡ አድልዎ፣ ትምክህት፣ ጥላቻ፣ ስም ማጥፋት፣ አለመቀራረብ ዋና ዋናዎቹ የመቻቻል ባህል እንቅፋቶች ናቸው፡፡

### ተግባር 5.4

1. ለመቻቻል ባህል ላለመዳበር እንቅፋት የሆኑ ሶስት ነገሮችን ጻፍ/ፊ፡፡
2. ለሰዎች የባህል፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖትና የአመለካከት ልዩነት በጎ አመለካከት ማጎልበት --------------ይባላል፡፡

## ማጠቃለያ

የመቻቻል ባህል ለሌሎች ሰዎች ሃሳብ፣ አመለካከትና ተግባር ፍቅርና አክብሮት ማኅልበት ነው፡፡ የመከባበር ባህል በማህበረሰብ ውስጥ ፍቅርና ሰላም ለማስፈን ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በርካታ ሰዎች የመቻቻልና መከባበርን ባህል በትምህርት ቤት፣ በማህበረሰቡና በእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ በተጨባጭ ሥራ ላይ ያለማዋል ጉዳይ ነው፡፡ አድልዎ፣ ትምክህት፣ ጥላቻ፣ ስም ማጥፋት፣ አለመቀራረብ ዋና ዋናዎቹ የመቻቻል ባህል እንቅፋቶች ናቸው፡፡

## የቃላት ፍቺ

- **መቻቻል:-** በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ማክበርና መቀበል መቻል ነው፡፡
- **መራራቅ -** አለመቀራረብ፣ አለመጣጣም
- **አድልዎ-** የሰውን ሀቅ ማዛባትና ማጭበርበር
- **ትምክህት-** እኔ እበልጣለሁ ወይም የእኔ ብቻ ይበልጣል ብሎ መገመትና ማሰብ
- **እንቅፋት-** መሰናክል

# የክለሳ ጥያቄዎች

**መመሪያ I. ትክክል ለሆነው ዓረፍተ-ነገር እውነት ስህተት ለሆነው ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ**

1. መቻቻል በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምና ፍቅር ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና አለው፡፡
2. የትምክህት ባህሪያት የመቻቻል ባህሪይ ከሚጠናከርባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡
3. የሌሎችን ባህል አለማክበር የህብረተሰብን ግጭት ያስከትላል፡፡
4. የመቻቻልን ባህሪይ የማይቀበሉ ሰዎች በመቻቻል ላይ እንቅፋት ይሆናሉ፡፡
5. መቻቻል ለአንድ ሃገር ዕድገት ወሳኝ ሚና አለው፡፡

**መመሪያ II. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. የመቻቻል ባህል አመልካች የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. የቋንቋ እኩልነት አለመኖር

   ለ. እኩል የመዳኘት መብት

   ሐ. የማሕበረሰብ እኩልነት መፍጠር

   መ. የፖለቲካ አመለካከት እኩልነት መፍጠር

2. ከዚህ በታች ከቀረቡት መካከል የመቻቻልን አስፈላጊነት የሚገልጸው የትኛው ዓረፍተ ነገር ነው?

   ሀ. አድልዎአዊነትን ማስፋፋት
   ለ. መቻቻል ሰላምና ፍቅርን በማስፈን ውስጥ ድርሻ የለውም ::
   ሐ.መቻቻል በማህበረሰብ መሀከል ግጭትን ያበረታታል፡፡
   መ. መቻቻል አንድነትን ያጠናክራል፡፡

3. የመቻቻል ባህል ለማጎልበት የሚያግዘው የትኛው ነው?

ሀ. ሰዎችን መከፋፈል
ሐ. መጣላት
ለ. እኩልነትን ማክበር
መ. የመቆጣት ባህርይ

መመሪያ III. ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. የመከባበር ባህል ማለት ምን ማለት ነው?
2. የመከባበር ባህልን እንዴት መጎናጸፍ ይቻላል?

# ምዕራፍ 6

# የባህል ብዝሃነትን ማክበር

## መግቢያ

በምዕራፍ አምስት ስለ መቻቻል ተምረሃል/ሻል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ የባህላዊ ብዝሃነት ምንነት፣ ባህላዊ ብዝሃነትንና ባህላዊ ብዝሃነትን የማስተናገድን አስፈላጊነት ትማራለህ/ሽ።

**የምዕራፉ የትምህርት ውጤቶች:-**

- የባህል ብዝሃነት ምንነትን ትገልጻለህ/ሽ፣
- የባህል ብዝሃነት አስፈላጊነትን ትዘረዝራለህ/ሽ፣
- የባህል ብዝሃነትን ታከብራለህ/ሽ ።

# 6.1. የባህል ብዝሃነትን ማክበር

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ :-

- የባህላዊ ብዝሃነትን ምንነት ትገል (ጸ)ለህ/ሽ፣
- የባህላዊ ብዝሃነት ጥቅሞችን ትገል (ጸ)ለህ/ሽ፣
- ባህላዊ ብዝሃነትን ታደንቃለህ/ሽ።



## የማንዛቤ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ቃላቶች ትርጉማቸውን ጻፍ:-

- የባህል ብዝሃነት
- ብዝሃነት
- የባህል ብዝሃነትን ማክበር
- መድልዎ

የባህል ብዝሃነት ማለት ብዙ ባህል ያለው ማህበረሰብ ማለት ነው። ማህበረሰብ የተለያየ ህብረተሰብ ልዩ ልዩ ባህል ይዘው አብረው በጋራ የሚኖሩ ሲሆን እነ (ዚ)ህ ማህበረሰቦች የተለያዩ ባህሎች ቋንቋ ፣ ሀይማኖት ፣አመለካከቶች ያላቸው ናቸው፡፡ በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ የተለያዩ የሃይማኖት፣ የቋንቋ እና የብሔር ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህም የባህል ብዝሃነት ምሳሌ ነው። በአገራችን ብዙ ቋንቋዎች (የተለያዩ ሃይማኖቶች ልምዶች እና ወጎች መኖራቸው ለባህል ብዝሃነት አርአያነቱ ተጨባጭ ምስክር ነው። ባህላዊ ብዝሃነት ያላት አገር ከተለያዩ ቀለማት እንደ ተሰራች ቅርጫት ታምራለች። ስለዚህ ባህላዊ ብዝሃነትን ማክበር ለባህል ልዩነቶችና ተግባራት አዎንታዊ አመለካከትን ያሳያል።



ምስል 6.1፡ የአገራችን ብዝሃነትን የሚያሳይ

ስለ ባህል ብዝሃነት የተዘጋጀዉን ጽሑፍ ካነበብክ በኃላ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ። ሁሉም ሰው በተፈጥሮው የተለየ ነው።እነዚህም ልዩነቶች በማህበራዊ በባህል በቋንቋ፣ በታሪክ፣ በአለባበስ፣ በምግብ፣ በብሔር፣ በሃይማኖት እና በመሳሰሉት ሊገለጹ ይችላሉ። የባህል (ብዝሃነት) የአብሮነትና የመካባበር ማሳያ ነው።

በእነዚህ ልዩነቶች ውስጥ ግንኙነቶችን መፍጠርና በሰላም አብሮ መኖር ይቻላል። ይህም ሰዎች እርስ በርሳቸው አዳዲስ ሀሳቦችንና አመለካከቶችን እንዲማሩ ዕድል ይሰጣቸዋል። የተለያየ ባህል ያላቸዉ ማህበረሰቦች ከሌሎች የባህል ስብጥር ካላቸዉ ሰፊ ክህሎት እና እውቀት ማግኘት ይችላሉ። በዚህ ልዩነት ውስጥ አንዱ የሌላውን ባህላዊ ቅርስ፣ ጥበብንና የባህል ውበት እውቅና መሰጠት ያስፈልጋል። እነዚህን ልዩ ልዩ ባህሎች ማወቅና ማስተናገድ እድለኝነት ነው።

ለተለያዩ ባህሎች ተገቢውን አክብሮት አለመስጠት እና ልዩነቶችን አለመቀበል

ችግር ልፈጥር ይችላል። ልዩነቶችን አለመቀበልና እዉቅና ኣለመሰጠት ግጭቶችንና አለመስማማቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናል፡፡ አንዳንድ ሰዎች የባህል ልዩነቶችን ያከብራሉ። ሌሎች ደግሞ የራሳቸውን ባህል ብቻ ያከብራሉ ያጎላሉ። ይህም ወደ ኣድልዎና ኣላስፈላጊ ግጭቶች ያመራል፡፡ ይህንን ለማስቀረት የባህል ብዝሃነትን በማክበር ላይ ቁርጠኛ ስራ መሰራትን ይጠይቃል። ስለሆነም ሁሉም ሰው እና የሚመለከታቸው አካላት የባህል ብዝሃነትን በማክበር ለጋራ ጥቅም መስራት መቻል አለባቸው።

## ተግባር 6.1

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያቹ በኃላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አድርጉ**

1. ባህላዊ ብዝሃነት በምን መንገድ ልገለጽ ይችላል?
2. ልዩነቶችን አለመቀበል ምን አይነት ችግር ሊያስከትል ይችላል?

## 6.2. በባህል ልዩነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

- በባህል ብዝሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነትን ትገልጻለህ/ሽ
- በልዩነት ዉሰጥ አንድነት ምን እንደሆነ ታብራራለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

- በባህል ብዝሃነት ውስጥ አንድነት ለምን ያስፈልጋል?
- ከሚከተለው ምስል ምን ተረዳ?



ስዕል 6.2. አንድነት ሃይል ነው

አንድነት ሃይል ሲሆን ባህላዊ ብዝሃነት ደግሞ ውቤት ነው። ስለዚህ ባህላዊ ብዝሃነት በማህበረሰቦች መካከል አንድነትን ለማጠናከር፣ ለውቤት፣ ለእኩልነት እና ለሰላም አስፈላጊ ነው። አንድነት በሰዎች መካከል የባህል ብዝሃነትን መረዳትና በመቀበል ጥሩ ግንኙነት እንዲፈጠር ይረዳል። አንድነት በሰላም አብረን እንዲንኖርና እንዲንሰራ ይረዳናል።

ስለዚህ አንድነት በባህል ብዝሃነት ውስጥ በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰብ ውስጥ የሰዎችን አብሮ የመኖር ፍላጎትን ይጨምራል ። እንዲሁም በሰዎች መካከል የተሻለ ቅንጅት፣ ግንኙነትንና የቡድን ስራን ያበረታታል።

በባህል ብዝሃነት ውስጥ አንድነት የተለያዩ ችግሮችን ያቃልላል። ለምሳሌ

በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ግለሰቦች በተናጥል ሊያደርጉት ማይችሉትን ችግሮች የሚፈቱት በመደጋገፍ ፣ በመተባበር ነው።



ስዕል 6.3: ማህበረሰቡ በመተጋገዝ ችግሮችን መፍታት

## ተግባር 6.2

በአካባቢያቹ የሚገኘውን የመረዳዳትና በመተጋገዝ ባህል ላይ ተወያዩ።

### ትረካ

በአንድ ወቅት አራት ልጆች ያሉት አንድ አባት ነበሩ ይባላል። አራቱም ልጆቻቸው አይስማሙም ነበር። አባታቸው በጠና ታመው የልጆቻቸው ሁኔታ ያስጨንቃቸው ነበር ። አባታቸው ልጆቹን ሊመክሩአቸው ፈልገ ወደ እራሳቸው ጠሯቸው። ልጆቹም ሲደርሱ ብዙ እንጨቶችን ሰብስቦ በየተራ እንዲሰብሩ ስጠይቃቸው አራቱም ልጆች አንድ ላይ የተሰበሰቡትን እንጨቶች መስበር አልቻሉም።በመጨረሻም ታናሹ ልጃቸው እንጨቶችን እየለየ አንድ በአንድ ይሰብራቸው ጀመር።

የልጆቹ አባት፣ "አያችሁ ልጆቼ፣ ከእናንተ አንዳችሁ እነዚህን አንድ ላይ ታሰረው ሳሉ እንጨቹን መስበር አልቻላችሁም።እንጨቶቹ ሲፈቱና ሲለያዩ

ግን በቀላሉ ትሰብሩታላቹ። “አሁን ገብቷቸዋል? እናንተም ሲትለያዩና ሳትስማሙ ሲትቀሩ የማታውቁት ሰው እንዲሁ በቀላሉ አንድ በአንድ ለየብቻ ለይቶ ሊጎዳቹ ይችላል። ነገር ግን ተስማምታቹ አንድ ብትሆኑ ማንም ሊያለያያችሁ አይችልም።” ልጆቹም ከዚያን ቀን ጀምሮ ተስማምተው አብሮ መኖር እንደቀጠሉ ይነገራል።





ስዕል 6.3፡ ከተባበሩና ከተጋገዙ ለውጤት ይደርሳሉ

## ተግባር 6.3

- ከላይ ከተገለ ጸው ትረካ ምን ተማራችሁ?

በአጠቃላይ  በባህል  ብዝሃነት  ውስጥ የአንድነት ጥቅሞች፡-

- አብሮ የመኖር ስሜትን ይጨምራል።
- የሰዎችን ግንኙነት እና ትብብርን በማበረታታት ምርታማነትን፣ የስራ ጥራትንና  የአኗኗር ዘይቤን ያሻሽላል።
- ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ይረዳል።
- የሰብአዊ መብቶችና  እኩልነትን  ለመጠበቅ ይረዳል.
- ለአንድነት ግንባታ ትልቅ ሚና ይጫወታል።
- የአገር  ባህላዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ ይረዳል።

## ተግባር 6.4

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ከተወያያችሁ  በኋላ  የዉይይቱን ውጤት ለጓደኞቻችሁ  ሪፖርት አድርጉ።

1. በባህል ብዝሃነት ውስጥ አንድነት ማጣት የሚያስከትለውን ውጤት ግለጽ/ጭ
2. በባህል ብዝሃነት ውስጥ አንድነት ስላለው ጠቀሜታ ሁለት ነጥቦችን ጻፍ/ፊ

## 6.3. በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል ጥቅሞች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

- የመቻቻል ጥቅሞችን ትገልጻለህ/ሽ።
- የሌሎችን ባህል ታከብራለህ/ሽ።
- የባህል ልዩነቶችን ታደንቃለህ/ሽ።

መቻቻል ማለት አንድን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ባለበት ሁኔታ አክብሮት በመስጠት ማስተናገድ ነው። የሌሎችን እምነት፣ የኑሮ ዘይቤና አመለካከትን ማክበር ማለት ነው። ይህም እርስ በርስ ለመከባበር፣ ለመረዳዳት፣ ለመተሳሰብ፣ ለመማማር፣ በሰላም አብሮ ለመኖር፣ ልማትን ለማፋጠን፣ ፍቅርን ለማጠናከር ያግዛል።

የኦሮሞ ህዝብ የተለያዩ ብሔሮች፤ ብሄረሰቦችንና ሕዝቦችን ባህል በማክበር እና እውቅና በመስጠት ይታወቃል። በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ እንኳን የሰው ልጅ ባህል የዱር አራዊትም ይከበራል። ይህ የሕዘቡ መገለጫውና እሴቱ ነው።

### ጉዳይ ጥናት፡- የትምህርት ቤት ጓደኞች

ኢፍቱ፣ ቶላሳ እና ቀጄላ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ከልብ የሚዋደዱ ጓደኞች ነበሩ። ኢፍቱ ሙስሊም ሲትሆን ቶሎላሳ ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታይ ነው፡፡ ቀጄላ ደግሞ የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታይ ነው። እነዚህ ተማሪዎች በጣም ይዋደዳሉ፡፡ ሁሉም መልካም ስነምግባርን የተላበሱ ናቸው። መምህራኖቻቸውንም ያከብራሉ፡፡ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በስነምግባር አርአያ ናቸው። በትምህርታቸውም ጎበዞች ነበሩ ። በበዓል ቀናትም አብሮ ያሳልፋሉ፡፡ ለምሳሌ የሙስሊም በዓላትን በኢፍቱ ቤት አብረው ያሳልፋሉ። በገና በዓል ደግሞ ኢፍቱ ደስታቸውን ለመካፈል ወደ ጓደኞቿ ወደ ቶላሳ እና ቀጄላ ቤት ትሄድ ነበር። ሌሎች ተማሪዎች በድርጊታቸው በጣም ይደሰታሉ። እንደእነሱ ለመሆንም ይጥራሉ። በተለይ በኢሬቻ በዓል አከባበር ሥርዓት

ሶስቱም የኦሮሞን የባህል ልብስ በመልበስ አብረው በደስታ ያሳልፋሉ። ቤተሰቦቻቸው በተማሪዎቹ ድርጊት በጣም ይደሰታሉ። ኢፍቱ፣ ቶሎሳ እና ቀጄላ ሁሌም "የሀይማኖት ልዩነታችን ውቤታችን ነው!" ይላሉ።

## ተግባር 6.5.

1. ልዩነት አብሮ መኖርን ይገድባል?
2. ከኢፍቱ፣ ቶላሳ እና ቀጄላ ድርጊት ምን ተማርክ/ሽ?



ምስል 6.5፡ የተለያየ ባህል ያላቸው ተማሪዎች በአንድነት

## ተግባር 6.6

1. ከዚህ ትረካ ምን ተማራችሁ?
2. ይህ ትረካ የባህል ብዝሃነት ማክበርን እንዴት ይገልጻል?

# 6.4. የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-**

- የባህል ብዝሃነትን ታደንቃለህ/ሽ።
- የባህል ብዝሃነትን ታከብራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

**በክፍል ውስጥ የባህል ብዝሃነትን እንዴት ታስተናግዳለህ/ሽ ?**

የሚንኖርባት ዓለም በልዩነት የተሞላች ናት። ይህ ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ልዩንነትን መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡ የሀገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችም የየራሳቸው ባህል አላቸው። ለረጅም ዘመናት አንዱ የሌላውን ባህል በማክበር አብረው ኖረዋል:: ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ የመከባበር፣ የመረዳዳት፣ የመተባበር እና በራስ የመተማመን ባህላቸውን አሳድጎላቸዋል። እንዲሁም የመግባባት ባህልንም ፈጥሮላቸዋል።

የባህል ብዝሃነት ለትምህርት ቤቶች ውቤት ነው። ከተለያዩ ባህል የመጡ ተማሪዎች ሲሰባሰቡ ቋንቋን፣ አዲስ እውቀትን፣ የአስተሳሰብ መንገዶችንና ልምዶችን ይጋራሉ። በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች የባህል ብዝሃነት ሲኖራቸው ከተለያዩ ብሔሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖቶች ጋር ለመላመድ ዕድል ይሰጣቸዋል።







ምስል፡ 6.6፡ የባህል ኤግዚቢሽን

## ተግባር 6.7

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አድርጉ።

1. የባህል ብዝሃነትን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው?
2. ልዩነትን መቀበል ለማህበራዊ ትስስር አስተዋፅዖ ያደርጋል ብለህ ታስባለህ/ሽ?

### ጉዳይ ጥናት 2፡ ባህላዊ ጭፈራ

መምህር ጉርሜሳ በቦኩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ4ኛ ክፍል የስነ-ምግባር መምህር –ናቸው። በባህል ብዝሃነት ውስጥ መቻቻልን ካስተማሩ በኋላ ለተማሪዎቻቸው –የቤት ስራ ሰጧቸው ። የቤት ሥራው ተማሪዎች ስለባህላዊ ውዝዋዜ ቤተሰቦቻቸውን ጠይቆ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ነበር። ተማሪዎቹም የተሰጣቸውን የቤት ስራ ይዘው ሲመጡ መምህራቸው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ አደረጉ። ተማሪዎቹም ተራ በተራ አቀረቡ። ጭፈራዎቹ ሲቀርቡ የሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች እንዲሳተፉ እና እንዲመለከቱ ተጋብዟል። የቀረበው ውዝዋዜ የተለያዩ ክልሎችን ባህል ያካተተ ስለሆነ በጣም አስደሳች ነበር። ሲመለከቱ የነበሩት ተማሪዎችም በጣም ደስተኞች ነበሩ። ጭፈራውና ውዝዋዜው የማይረሳና ሁሉም ተማሪ የሚያስታውሰው ጊዜ ነበር። ተማሪዎች የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ውዝዋዜና ጭፈራ በማየታቸው ዝግጅቱን የበለጠ ወደውታል።

## ተግባር 6.8.

- ከተማሪዎቹ ውዝዋዜና ጭፈራ የተማራችሁትን በመወያየት ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ማጠቃለያ

የባህል ብዝሃነት ማለት የተለያየ ባህል ያለው ማህበረሰብ አብሮ መኖር ነው። ብዝሃነትን ማክበር የተለያየ ባህል ላለው ማህበረሰብ እውቅና ሰጥቶ በሰላም አብሮ መኖር ነው። ብዝሃነትን በእኩልነት ማክበርና ማስተናገድ ከባህላችን ተጠቃሚ እንድንሆን ያደርገናል።

የኦሮሞ ሕዘብ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ባህል አክብሮ አብሮ በመኖር ይታወቃል። በኦሮሞ ሕዘብ ዘንድ የሰው ባህል ብቻ ሳይሆን የዱር አራዊትም ይከበራል። ይህ የሕዝዘቡ መገለጫና እሴት ነው። የባህል ብዝሃነት ጥቅሞች ብዙ ናቸው፡፡እነሱም መከባበር፣ መረዳዳት፣ እኩልነት፣ ፍትህ እና ፍቅርን ያጎለብታል፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱን እድገት ያፋጥናል። የሌሎች ሰዎችን ባህል አለማክበርና እውቅና አለመስጠት ግጭትን ያስከትላል፡፡ ይህ ወደ ሰላምና መረጋጋት እጦት ያመራል፡፡ ስለዚህ የባህል ብዝሃነትን በማክበር፣ መቻቻልንና ፍቅርን ማሳደግ የሀገርን እድገት ያፋጥናል።

## የቃላት ፍቺ

- **ብዝሃነት፡-** የማህበራዊ ኑሮ፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል፣ የአመለካከት ብዝሃነትን ያጠቃልላል፡፡
- **የባህል ብዝሃነትን ማክበር ማለት የሃይማኖት፣** የቋንቋ፣ የብሔር ወይም ሌላ ልዩነት ካለው ማህበረሰብ ጋር ተስማምቶ መኖርን ያመለክታል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

**መመሪያ 1፡ ትክክል የሆነዉን ዓረፍተ ነገር እውነት ትክክል ያልሆንውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. የባህል ብዝሃነት ለሀገር እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል።
2. ብዝሃነትን ስናከብር ከባህላችን ተጠቃሚ መሆን እንችላለን።
3. የሌሎችን ባህል አለማክበር የባህል ብዝሃነት ባላቸው ህብረተሰብ መካከል ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡
4. የባህል ብዝሃነትን ማክበር እና የተለያዩ ብሔር ብሂረሰቦችን ባህል በእኩልነት ማስተናገድ አስፈላጊ ነው።

**መመሪያ II.** በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ካነበብክ/ሽ በኋላ መስማማትህን/ሽን እና አለማስማማትህን/ሽን በ "√"ምልክት አሳይ።

| ተ/ቁ | ሀሳቦች | እስማማለው | አልስማማም |
|---|---|---|---|
| 1 | ከሌሎች ሰዎች ጥሩ ልምዶችን ማግኘት እችላለሁ | | |
| 2 | በቤተሰቦቼና በባህሎቼ እኮራለሁ | | |
| 3 | በቤተሰቤ እና በትምህርት ቤት የሰላም አርአያ እሆናለሁ። | | |
| 4 | የማህበረሰቡን ባህል ከሚጎዱ ድርጊቶች እርቃለሁ። | | |
| 5 | ልጆች የራሳቸው የሆነ መገለጫ እንዳላቸው አምናለሁ። | | |
| 6 | ልጆች በባህላቸው ሊወደዱ እና ሊከበሩ እንደሚገባቸው አምናለሁ። | | |
| 7 | ተማሪዎች እንዲወዱኝና ጥሩ ጓደኛ እንዲሆኑልኝ እፈልጋለሁ ። | | |
| 8 | በትምህርት ቤቴ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ባህል የሚችለውን ያህል እማራለሁ። | | |

**መመሪያ III.** ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩበት

1. ልዩነትን ማክበር ምን ምን ጥቅሞች አሉት?
2. አድልዎ ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ምን ምን እርምጃዎችን መውሰድ እንችላለን?